ውስጥ ሊኖር በሚገባው ዕድገትና ውጤታማ አመራር ላይ ያስከተለውን ችግር ግለጹ:: ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመካከላቸው በመዋደድና በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲኖር ሊያደርጉ የሚችሏቸውን ነገሮች ዘርዝሩ:: መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከምእመናን ጋር በመዋደድና በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት እንዲኖር ሊያደርጉ የሚችሏቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ሠ) ግንኙነትን ለማሳደግ ያስችላሉ ተብለው በዚህ ትምህርት ውስጥ የቀረቡትን ስድስት መንገዶች ብንከተል፣ ይህ በሰዎች መካከል የሚኖረውን አመኔታ እንዴት ያሳድገዋል?

2. ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች ባለፈው ዓመት ለመወሰን የተገደዱባቸውን ሦስት ከባባድ ውሳኔዎች ዘርዝሩ:: ለ) በዚህ ዓመት የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች የተጋፈጧቸውን ሦስት አደገኛ ውሳኔዎች ግለጽ:: ሐ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች በዚህ ዓመት ለመፍታት የተገደዱባቸውን ሦስት ችግሮች ግለጽ:: መ) መሪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ ማስታወስ ያለባቸውን መሠረታዊ መርሖዎች ከልሱ:: እያንዳንዱ መርሕ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? መሪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ እያንዳንዱን መርሕ ካልተከተሉ ምን ችግር ይከሰታል? ሠ) የተሰመዱት ወጥመዶች መሪዎች ጥሩ ውሳኔ እንዳያደርጉ ሲገድቡ የተመለከታችሁት እንዴት ነው?

3. ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ የተጋፈጠችውን ዓቢይ ውሳኔ ግለጹ:: ለ) በአንድ ሁኔታ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለ ማወቅ በዚህ ትምህርት ውስጥ የተሰጡትን ነጥቦች በመጠቀም፣ ለዚህ ውሳኔ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት ማወቅ እንደሚቻል ተወያዩ:: ሐ) ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአንድ ጉዳይ ላይ የእግዚእብሔርን ፈቃድ በመሻት በቂ ጊዜ ያሳልፋሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? ካልሆነ፣ ለምን? የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ሳይሞክሩ የተሻለ የሚመስላቸውን ውሳኔ የሚሰጡ ከሆነ፣ ምን ዓይነት አሉታዊ ነገሮች ይከሰታሉ?



4. አንድ መሪ ወይም ቦርድ ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት መከተል ያለባቸውን ደረጃዎች ከልሱ:: እነዚህ ደረጃዎች ለምን አስፈላጊ እንደ ሆኑ አብራሩ::

# ትምህርት አሥራ ሦስት

## አንደኛ ቀን

ባለፈው ሳምንት የአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ውጤታማነት ጥሩ ውሳኔ በመስጠት ከህሎቱ ላይ እንደሚደገፍ አጥንተናል:: አንድ መሪ አስቸጋሪ ውሳኔ ለመስጠት የሚፈራ፣ ወይም የቤተ ክርስቲያንን ውሳኔዎች በመምራት ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንድትደርስ የማያስችላት ከሆነ፣ እግዚአብሔር የሚጠብቅበትን መንፈሳዊ አመራር እየሰጠ አይደለም ማለት ነው:: ከዚህም በላይ የአስተዋይነት ውሳኔዎች መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ሌላም አንድ በጣም አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ አለ:: እነዚህም ቤተ ክርስቲያኒቱን በሚያስተዳድሩ ቦርዶች የሚሰጡ ውሳኔዎች ናቸው:: (ማስታወሻ፡- ጥሩ የቦርድ ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚያግዙ አሳቦች በትናንትናው ትምህርት ውስጥ ቀርበዋል::)

## ጥሩ የቦርድ ውሳኔዎችን እንዴት መስጠት እንደሚቻል

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቦርድ ስብሰባ ተካፍለህ ታውቃለህ? ለ) ከሆነ፣ ቦርዱ የተወያየባቸው ጉዳዮች በቤተ ክርስቲያን ላይ ለውጥ የሚያመጡ ጠቃሚ ጉዳዮች ነበሩ? ሐ) የሽማግሌዎች ቦርድ ዓላማ ምን ይመስልሃል? የአውራጃ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ ዓላማስ? |

ከቤተ ክርስቲያን ዐበይት ውሳኔዎች ብዙዎች የሚሰጡት በኮሚቴዎች ወይም በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች አማካኝነት ነው:: (ለምሳሌ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሚቴ፣ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ፣ የዞን የቦርድ ስብሰባዎች፣ ወዘተ. . .) ውሳኔዎችን ለመስጠት ኮሚቴዎችን ወይም ቦርዶችን መጠቀሙ በጣም ውጤታማ ወይም በጣም ጊዜ የሚያባክን ሊሆን ይችላል:: ብዙውን ጊዜ ቦርዶች በማይረቡ ጉዳዮች ላይ ሲከራከሩ ጊዜያቸውን ሙጥጥ አድርገው

ካጠፉ በኋላ፣ ወሳኝ የሆኑትን ጉዳዮች ለመወሰን የጥድፊያ እርምጃ ይወስዳሉ:: ወይም ደግሞ በቂ መረጃ ሳይኖራቸው በተሳሳቱ መረጃ ዎችና ግምቶች ተመርተው ስለማያውቁት ጉዳይ እርባና - የሌለው ውሳኔ ይሰጣሉ:: ከዚህም የተነሣ፣ አንዳድ ውሳኔዎች ጥበብ የጐደላቸው ስለሚሆኑ፣ የቤተ ክርስቲያን አባላት ውሳኔዎቹን አንቀበልም ይላሉ::

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች ከቦርድ ወይም ከኮሚቴ ጋር የሚሠራ የቤተ ክርስቲያን መሪ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ታስበው የቀረቡ ናቸው:: ስዎች በዚህ መንገድ በአንድነት በሚሠሩበት ጊዜ፣ የቡድኑ ጥበብ ለእግዚአብሔር የበለጠ ክብር በማምጣት ላይ ያተከረ ይሆናል:: (ማስታወሻ:- ከዚህ በታች የምናቀርበው አሳብ፣ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሽማግሌዎች ቦርድ፣ መሪው ቀጣናውን እንዲመራ ለማያግዝ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣ ወይም በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ላይ ለሚሠራ ማንኛ ውም ቦርድ ሊያገለግሉ ይችላሉ:: ነገሩን ለማሳጠር፣ በቤተ ክርስቲያን መሪው ላይ ሥልጣን ያለውን ማንኛውንም አስተዳደራዊ መዋቅር «ቦርድ» በሚለው ቃል እንጠራዋለን::)

1. ውክልና የተሰጣቸው ሰዎች ስለ ቦርድ ስብሰባዎች ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል:: ብዙውን ጊዜ ሽማግሌዎች የሚሰባሰቡት ስለ ስብሰባው ዓላማ በማሰብ ሳይሆን፣ በየወሩ መሰባሰብ ስላለባቸው ብቻ ነው:: ወይም ደግሞ የመጡት ሙሉ ግንዛቤ ይዘው ሳይሆን፣ በቦርዱ ላይ እንዲቀመጡ ስለ ተመረጡ ብቻ ሊሆን ይችላል:: በዋናነት፣ የቦርድ ስብስባ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ መወሰን አለበት። የቦርድ ስብሰባ ዎች ነገሮች በጥሩ ሁኔታ እንዲካሄዱ ከማድረጉ አስተዳደራዊ ተ ግባራት ያለፉ ሥራዎችን በማከናወን ለእግዚአብሔር ሕዝብ የመሪነት አገልግሎት መስጠት አለባቸው::

የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ አካላት ብዙውን ጊዜ አምስት ተ ግባራትን ያከናውናሉ::



ሀ. ውክልና የተሰጣቸው ሰዎች ቤተ ክርስቲያኒቱ ወይም አብያተ ክርስቲያናቱ ቦርዱ በተስማማው መንገድ መመራታቸውን ማ ረጋገጥ አለባቸው። የቤተ ክርስቲያኒቱን መሪ ቦርዱ በወሰነው አቅጣጫ ቤተ ክርስቲያኒቱን እንዲመራ ተጠያቂ ያደርጉታል:: ይሁን እንጂ፣ በመሪው ዝርዝር ሥራዎች ውስጥ ጣልቃ መግባት የለባቸውም። የሂሳብና የቤተ ክርስቲያን መሪው የሥራ ሪፖርት ዓላማ መሪው ቤተ ክርስቲያኒቱን ቀደም ሲል የሽማግሌዎች ቦርደ ወደ ወሰነው ግብ እየመራት መሆኑን ማሳየት መሆን አለበት:: በዚህ ጊዜ የቦርዱ አባላት መሪው እንዴት በተሻለ ሁኔታ ሥራውን እንደሚያከናውን ምክር ሊሰጡት ወይም ትክክል አይደለም ብለው ስለሚያስቡት ነገር ጥያቄዎችን ሊያቀርቡለት ይችላሉ::

ለ. ቦርዱ በቤተ ክርስቲያን-አቀፍ ስልታዊ ጉዳዮች ላይ ትኩ ረት ማድረግ አለበት:: ቦርዱ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ እንዲያከናውን ውክልና በሰጣቸው አስተዳደራዊ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም:: ይልቁንም፣ ቦርዱ ለቤተ ክርስቲያን ስልታዊ አቅጣጫ መቀየስና አፈጻጸሙን ለቤተ ክርስቲያን መሪው መተው አለበት:: በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም በአውራጃ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነሡትን ችግሮች ሁሉ መፍታት የቦርዱ ዓላማ አይደለም:: እንዲህ ዓይነት ችግሮች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ካስፈለገም በተወከሉ የቦርዱ አባላት መፈታት አለባቸው:: የቦርድ አባላት የሚሰባሰቡት የራሳቸውን አካባቢ በመወከል በተቻለ መጠን አካባቢያቸውን ለመጥቀም መሆን የለበትም:: እንዲህ ዓይነቱ ስብሰባ ከአንድነት ይልቅ መቀናናትንና መከፋፈልን ያስከትላል:: ይልቁንም፣ የቦርዱ ዓላማ በሁሉም አካባቢዎች የሚታዩትን የጋራ ችግሮች መፍታት መሆን አለበት:: ቦርዱ በስልታዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር፣ «እግዚአብሔር በጋራ ለክብሩ ምን እንድናደርግ እየጠራን ነው?» ለሚለው ዓይነት ጥያቄ መልስ ማግኘት አለበት:: ሰብሳቢው አጀንዳውን በመመልከት በአስተዳዳሪ ሊፈታ የሚችል ጉዳይ አለመካተቱን ማረጋገጥ አለበት::

ሐ. ቦርዱ ሁሉንም አካባቢዎች በሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ትኩረት መስጠት አለበት:: ለቤተ ክርስቲያን አባላት ዓመታዊ ክፍያ የመወሰን፣ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን የሙሉ ጊዜ ደመወዝ ተከፋይ መጋቢ እንድታገኝ፣ ወይም አገር አቀፍ ወንጌላውያን ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት ግንኙነት ማድረግ እንዳለባቸው የሚደነግጉ ውሳኔዎች መተላለፍ ካለባቸው፣ ቦርዱ እነዚህን ፖሊሲዎች ማውጣት አለበት:: ይህ የቤተ ክርስቲያቱ መሪ ቤተ ክርስቲያኒቱን በተደነገገው ደንብ መሠረት ለማስተዳደርና ተጠያቂ ለማድረግ ያስችላል::

መ. ቦርዱ ለቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ በጀት መመደብ አለበት:: ቦርዱ የቤተ ክርስቲያኒቱ ገንዘብ በምን ምን ጉዳዮች ላይ መዋል እንዳለበት ይወስናል:: መሪውም የእግዚአብሔርን ገንዘብ በአስተዋይነት መጠቀሙን በመከታተል በኃላፊነት ይጠይቀዋል:: ቦርዱ ዓመታዊ በጀት በሚያወጣበት ጊዜ፣ እያንዳንዱ አባል በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ኃላፊነቶቹን በመወጣት በጀቱን እውን ለማድረግ መስማማቱ ነው:: ቤተ ክርስቲያኖቻቸው የገንዘብ ግዴታ ዎቻቸውን እንዲወጡ ለማሳመን የሚቸገሩ ከሆነ፣ ይህም በበጀቱ ውስጥ መካተት አለበት:: ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ባለመስጠቷ ምክንያት በተግባር የማይገለጽ በጀት ማጽደቁ ጥቅም የለውም::

ሐ. የቤተ ክርስቲያ የበታች የአመራር አካላት ለመፍታት ሞክረው ያቃታቸው ማንኛውም ጉዳይ:: የቦርዱ ስብሳቢ የበታች የአመራር አካላት በሙሉ ችግሩን ለመፍታት መሞክራቸውን ማረጋገጥ አለበት:: ካልሆነ፣ ጉዳዩን ወደ እነርሱ መመለስ አለበት (ጉዳዩ የቦርድ አባላቱን ተሳትፎ የሚጠይቅ አጣዳፊ ነገር እስካልሆነ ድረስ):: ቦርዱ ከሥሩ ያሉትን መሪዎች ሥልጣን መናቅ የለበትም:: ከዚህ ይልቅ፣ ቦርዱ የበታች አመራር አካላት የሰጡትን ውሳኔ መመርመር አለበት:: ውሳኔው ለሁሉም አካላት ፍትሐዊ ነበር? ውሳኔውን ሊያስቀይር የሚገባ አዲስ መረጃ አለ? በውሳኔ አሰጣጡ ውስጥ የተከሰተና ውሳኔውን ሊያስቀይር የሚችል ከፍተኛ ስሕተት ነበር? ብዙውን ጊዜ ጉዳዮች ወደ ቦርዱ የሚመጡት አንደኛው አካል ውሳኔውን ለመቀበል ባለመፈለጉ ምክንያት ነው::



ቦርዱ ውሳኔው ፍትሐዊ መሆኑን ካረጋገጠ፣ ሁለቱንም ወገኖች የሚያስደስቱ መንገዶች ከማፈላለግ ይልቅ፣ ውሳኔውን ማጽደቁ ተገቢ ይሆናል:: የቦርዱ አባላት ሰዎች የማይፈልጓቸው ውሳኔዎች በሚገጥሟቸው ጊዜ ወደ ቦርዱ እንዲመጡ የሚፈቅዱላቸው ከሆነ፣ የመሪዎቻቸውን ውሳኔ ለመቀበል ፈቃደኞች ላይሆኑ ይችላሉ:: ይህም ቦርዱ የእርሱ ያልሆነውን ሥራ በማከናወን እንዲጠመድ ያደርገዋል:: ስለሆነም፣ ቦርዱ የበታች ኃላፊዎችን ውሳኔ ማጽደቅ፣ የበታች ኃላፊዎች ውሳኔ የተሳሳተ ነበረ ብለው የሚያምኑ ከሆነ ደግሞ፣ ውሳኔ የሚስጥባቸውን ሌሎች መንገዶች ማቅረብ አለበት:: ብዙውን ጊዜ ቦርዱ የበታች አመራር አካላት ያልተስማሙባቸውን ጉዳዮች ለመፍታት የሚያስችል በቂ ጊዜና መረጃ አይኖረውም:: በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ሥራዎች መከናወን ካለባቸው፣ ቦርዱ ንዑስ ኮሚቴ ወክሎ ሥራውን ማከናወን ይችላል::

የቦርዱ አባላት አጠቃላዩ ድርጅት (ቤተ ክርስቲያን፣ የአውራጃ ቤተ ክርስቲያን፣ ቀጣና እና አገር አቀፍ) እግዚአብሔር የሰጣትን ራእይ እየፈጸመች መሆኗን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው:: ምንም እንኳን የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን በመወከል ከተለያዩ አካባቢ ዎች ቢሰባሰቡም፣ የተሰባሰቡት ለቤተ ክርስቲያኖቻቸው ለመናገር ወይም ቤተ ክርስቲያኖቻቸውን ለመጥቀም አለመሆኑን መረዳት አለባቸው:: ይልቁንም፣ የአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንን ችግሮች በመመልከት ለሁሉም የሚጠቅሙ ውሳኔዎችን የመስጠት ኃላፊነት እንዳለባቸው መዘንጋት አይገባቸውም:: ከመጡበት ቤተ ክርስቲያን ጋር የተያያዙ የየራሳቸው አመለካከቶች ሊኖሯቸውና ውሳኔው በቤተ ክርስቲያናቸው ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ሊያስከትል እንደሚችል የመግለጽ ነጻነት አላቸው::: ነገር ግን ከትልቁ አካል ለአካባቢያቸው ቤተ ክርስቲያን ጥቅም ለማስገኘት እንደ ተለሳፊ አድርገው ራሳቸውን መመልከት የለባቸውም:: መጠየቅ ያለባቸው ትልቁ ጥያቄ «ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚሻለው የትኛው ነው?» የሚል መሆን አለበት::

2ኛ ጥያቄ:- ሀ) አምስቱን ዋና ዋና የቦርድ ኃላፊነቶች አብዛኞቹ የሽማግሌዎች ወይም የአውራጃ ቦርዶች ከሚወያዩባቸው ነገሮች ጋር አነጻጽር። የሚለያዩትና የሚመሳሰሉት እንዴት ነው? ለ) ለቦርድ አባላት ሚናቸው ምን እንደ ሆነ መረዳታቸው ምን ይጠቅማል?

2. ውጤታማ የውሳኔ ሰጭነት ሂደት የሚኖረው መሪውና ቦርዱ ሥልጣናቸውን በትክክል ሲረዱ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪው ቦርዱ በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ እንደ ወከለውና የትኞቹን ጉዳዮች ለቦርዱ ማስተላለፍ እንዳለበት ማወቅ አለበት። የቦርድ አባላቱም የትኞቹ ጉዳዮች ወደ እነርሱ መጥተው መጽደቅ እንዳለባቸውና የትኞቹ በመሪው ማለቅ እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ የሥልጣን ዳርቻዎቻቸውን በግልጽ በማይገነዘቡበት ጊዜ ሁለት ችግሮች ይከሰታሉ:-

<u>አንደኛ</u>፣ በቤተ ክርስቲያን መሪው ማለቅ የሚገባቸው ብዙ ውሳኔዎች አላግባብ ወደ ቦርዱ ይተላለፋሉ። ይህ ቦርዱ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ እንዲሰጥ ስለሚያስገድድ፣ የቦርዱን ጊዜ ይሻማል። በተጨማሪም ቀላል ጉዳይ ነው ብለው በማሰብ የቦርዱን ውሳኔ የሚጠባበቁትም ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለሚወስድባቸው ይናደዳሉ።

<u>ሁለተኛ</u>፣ በተለያዩ የአመራር ደረጃዎች መካከል ውጥረት ይነግሣል። ለዚህም ምክንያቱ ውሳኔዎችን እኔ ማጽደቅ አለብኝ የሚል ስሜት መፈጠሩ ይሆናል። የቦርዱ አባላት እኛ ውሳኔ ልንሰጥበት ይገባል በሚሏቸው ጉዳዮች ላይ መሪው ውሳኔ የሰጠ እንደ ሆነ ይበሳጫሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪውም ኃላፊነቴ ነው ብሎ በሰጠው ውሳኔ ምክንያት ተግሣጽ በሚደርስበት ጊዜ ይከፋል።

በአጠቃላይ፣ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የቤተ ክርስቲያንን ወይም የአውራጃ ቤተ ክርስቲያንን ዝርዝር ገዳዮች የማስተዳደር ኃላፊነት ሊሰጠው ይገባል። ገንዘብ መክፈል፣ ለቢሮ የሚያስፈልጉትን ነገሮች መግዛት ወይም ገንዘብ ከባንክ ማውጣትን የመሳሰሉ ነገሮች ወደ ቦርዱ የሚመጡ ከሆነ፣ ሰዎች ቀላል ነገሮችን ለማስወሰን ብዙ ጊዜ ለመጠበቅ ስለሚገደዱ፣ ችግሮች



ይፈጠራሉ። ብዙውን ጊዜ እዚያው የሚገኙት መሪዎች እነዚህን የዕለት ተዕለት ተግባራት የማስተዳደር ሥልጣን ሊሰጣቸው ይገባል። ሊቀመንበሩ የመንግሥት ሠራተኛ በመሆኑ ምክንያት ለጉዳዮች ውሳኔ ለመስጠት በብዛት የማይገኝ ከሆነ፣ እዚያው ለሚገኙት የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ውክልና በመስጠት ውሳኔዎችን እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል።

*ለምሳሌ፣ ቦርዱ ወንጌላዊው ለገና በዓል ወደ ቤቱ መሄድ አለበት ወይ? የሚለውን ጉዳይ መወሰን የለበትም። ቦርዱ «አንድ ወንጌላዊ አገልግሎቱን ከሚሰጥበት አካባቢ መራቅ የሚችለው በዓመት ለሦስት ሳምንታት ብቻ ነው» የሚል ዓይነት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል። ይህም የወንጌላዊውን አገልግሎት የሚከታተለው የቤተ ክርስቲያን መሪ የቦርዱን መመሪያ በማይጥስ መንገድ ወንጌላዊው ወደ ቤተሰቡ ሊሄድ የሚችልበትን ሁኔታ እንዲረዳ ያስችለዋል።*

ሁሉም የአጀንዳ ጉዳዮች ቀደም ብለው ለቤተ ክርስቲያን መሪው መሰጠት አለባቸው። አንድ ጉዳይ ወደ ቦርዱ መቅረብ እንዳለበት ወይም እንደሌለበት መወሰኑ የሊቀ መንበሩ ኃላፊነት ነው።

እያንዳንዱ አጀንዳ በሦስት መንገዶች ሊስተናገድ ይችላል:-

ሀ. ስብሳቢው ለዚህ ጉዳይ ውሳኔ መስጠት የሌላ ሰው እንጂ የቦርዱ ኃላፊነት እንዳልሆነ ሊወስን ይችላል። (ለምሳሌ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤትን የሚከታተል ኮሚቴ ካለ፣ ጉዳዩ መሄድ ያለበት ወደ እርሱ ወይም ወደ ቦርዱ ሳይሆን፣ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ኮሚቴው ነው። ጉዳዩ ወደ ቦርዱ መሄድ ያለበት የፖሊሲ ለውጥ ካለ ብቻ ነው።) ቦርዱ ለሌሎች በውክልና የተሰጠውን ጉዳይ ለመወሰን መጣር የለበትም። ቦርዱ ለሌሎች በውክልና በተሰጡት ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ፣ እነዚህ ሰዎች የአመራር ክህሎታቸውን ሊያሳድጉ አይችሉም።

ለ. ሰብሳቢው ጉዳዩን መከታተል የራሱ ኃላፊነት እንደ ሆነ ሊወስን ይችላል። ይህ ከሆነ፣ ራሱ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን

ለጉዳዩ መፍትሔ መስጠት እንዳለበት መወሰን ይኖርበታል። አንድ ኮሚቴ ተቋቁሞ የውሳኔ አሳብ እንዲያቀርብለት ቢያደርግ ይሻል ይሆን? ወይስ እንደ ወንጌላዊ ወይም መጋቢ ካሉት ሌሎች አገልጋዮች ጋር በመሆን ውሳኔ ቢሰጥ ይሻል ይሆን? ለምሳሌ፣ ጉዳዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤትን የሚመለከት ከሆነ፣ ራሱ ውሳኔ ባይሰጥና ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ዳይሬክተርና ከሥነ-መለኮት ትምህርት ኮሚቴ ጋር በመተባበር መፍትሔ ቢያፈላልግ የተሻለ ይሆናል።

ሐ. ሰብሳቢው ጉዳዩ ወደ ቦርዱ እንዲሄድ ሊወስን ይችላል። በአጀንዳው ላይ መስፈር ያለባቸው እንደ ፖሊሲ ጉዳዮች ወይም ከሰብሳቢው የአስተዳደር ሥልጣን ያለፉ ጉዳዮች ብቻ መሆን አለባቸው። ያን ያህል አስፈላጊ ያልሆኑትን ጉዳዮች ወደ ቦርዱ የሚያስተላልፍ ከሆነ፣ የቦርድ ስብሰባው ሰብሳቢው ሊወስናቸው በሚገቡ ጉዳዮች ይጣበባሉ ማለት ነው። ይህ ደግሞ ቦርዱ አስፈላጊዎቹን ጉዳዮች ለመወሰን በቂ ጊዜ እንዳያገኝ ያደርጋል።

ቦርዱ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ደረጃ የሚነሡትን ጉዳዮች የመዳኘት ኃላፊነት እንደሌለው መገንዘብ አለበት። እንዲህ ዓይነት ጉዳዮችን ለማስተካከል ቦርዱ ጥረት ማድረግ ያለበት የበታች አካላት የሚችሉትን ሁሉ አድርገው ችግሩ ካልተፈታና በአግባቡ ወደ ቦርዱ ከተመራ ብቻ ነው። እንዲሁ ደግሞ ውሳኔውን ለመስጠት የሚያስችል መረጃና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች በሙሉ ወደ ቦርዱ መቅረብ አለባቸው።

4. የቦርዱ አባላት ጊዜ ሳያባክኑ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጡ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ማዘጋጀት የሰብሳቢው ኃላፊነት ነው። ብዙውን ጊዜ የቦርድ አባላት በራሳቸው አገልግሎቶች የተጣበቡ በመሆናቸው፣ ጊዜያቸው ውድ ነው። ስለዚህ፣ ሰብሳቢው ጊዜ ያቸው እንዳይባክን ጥረት ማድረግ አለበት።

በታችኞቹ የአስተዳደር እርከኖች በቂ ውይይት ያልተደረገበትና አስተያየት ያልተሰጠበት ጉዳይ ወደ ቦርዱ መቅረብ የለበትም። ብዙውን ጊዜ በአገልግሎቱ ውስጥ የሚሳተፉት የቦርድ አባላት አይደሉም።



የቦርዱ አባላት ጉዳዩን ስለማያውቁት፣ ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል መረጃና ተሞክሮ ላይኖራቸው ይችላል። ስለሆነም፣ መረጃውና የጉዳዩ ተሞክሮ ያላቸው የታች የአመራር አካላት በሚገባ ተወያይተው አስተያየታቸውን ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው። ይህም ቦርዱ የውሳኔ ሂደቱን ከመጀመሪያው ከመጀመር ይልቅ በአስተያየቱ ላይ እንዲወያይ ያስችለዋል።

ቦርዱ አስተዋይነት ያለው ውሳኔ ለመስጠት እንዲችል፣ ሰብሳቢው እያንዳንዱን አጀንዳ በሚከተሉት መስፈርቶች መሠረት መመርመር አለበት:-

ሀ. ይህ ቦርዱ ሊወያይበት የሚገባው አጣዳፊ ጉዳይ ነው? ሰብሳቢው አጀንዳውንና አሁን ውሳኔ ባይሰጥ የሚመጣውን ችግር በሚገባ መመርመር አለበት። አሁን ውሳኔ ካልተሰጠ፣ ነገሮች እየተባባሱ ይሄዳሉ? እንደዚያ ከሆነ፣ ጉዳዩ በአጀንዳነት ተይዞ ለቦርዱ መቅረብ አለበት። ጉዳዩ እየባሰ የሚሄድ ዓይነት ከሆነ፣ ለሌላ ስብሰባ ከማቆየት ይልቅ አሁኑኑ ለውይይት ማቅረቡ የተሻለ ነው። ብናቆየውና ችግሩ እየከፋ ቢሄድ፣ መፍትሔ ለማግኘት የሚኖረን አማራጭ በጣም አነስተኛ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ጉዳዩ የሚያስቸኩል ካልሆነ፣ ሰብሳቢው ቅድሚያ ትኩረት በማይሰጣቸው አጀንዳዎች ዝርዝር ውስጥ ሊያስፍረው ይችላል። ለዎች ጥሩ ውሳኔ የሚሰጡት ብዙውን ጊዜ አስፈላጊነቱን ሲረዱ ነው።

ለ. ጥራት ያለው ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎች በሙሉ ተሰባስበዋል? ሰዎች ምንም ስለማያውቁት ጉዳይ ውሳኔ ለመስጠት ቢሞክሩ፣ ዋጋ የለውም። አንድ ቦርድም በቂ መረጃ ሳይኖረው ውሳኔ ቢሰጥ፣ ውጤቱ አደገኛ ይሆናል። በግምት የሚሰጥ ውሳኔ በአመዛኙ የከፋ ውጤት ያስከትላል። ሁሉም አስቸጋሪ ውሳኔዎች አደገኞች ናቸው። ለዚህም ምክንያቱ ሁሉንም መረጃ ማግኘቱ አስቸጋሪ መሆኑና ሰዎች ምን ዓይነት ምላሽ እንደሚሰጡ ስለማናውቅ ነው። ነገር ግን ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉትን መረጃዎች ካሰባሰብን፣ አደጋውን ልንቀንስ እንችላለን።

ሐ. ስለ ጉዳዩ ሙያዊ ችሎታ ያላቸው ወይም በጉዳዩ ውስጥ የተሳተፉ ወይም ተሞክሮው ያላቸው ሰዎች ጥናት አድርገው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል? ብዙውን ጊዜ ጊዜው ያላቸውና በተነሣው ችግር ላይ ልምድ ያላቸው ሰዎች በመጀመሪያው አካባቢ ጉዳዩን በመመርመሩ ረገድ ተሳታፊ ቢሆኑ መልካም ነው:: እነዚህ ስለ ጉዳዩ እውቀቱ ያላቸው ሰዎች ምርመራ አድርገው ለቦርዱ የራሳቸውን አስተያየት መስጠት አለባቸው:: ስለሆነም፣ እንደ መጋቢዎች፣ ወንጌላውያንና የሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች ያሉ ወገኖች ካሉ፣ በአገልግሎታቸው አካባቢ የመጀመሪያ ዕቅዶችን በማውጣቱ ላይ መሳተፍ አለባቸው:: እነዚህ ሰዎች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ተወያይተው መልሶችን ለቦርዱ እንዲያመጡ መጠየቁ ተገቢ ይሆናል::

1) ውሳኔ የሚያሻውን ጉዳይ፣ ወይም ችግር፣ ወይም ግብ በአጭሩ መግለጽ አለባቸው::

2) መፍትሔ ይሆናሉ የሚሏቸውን አያሌ አሳቦች መስጠት አለባቸው::

3) የውሳኔ አሳቦቻቸውን ጠቅለል አድርገው ሊያዘጋጁና ይህንኑ የውሳኔ አሳብ የመረጡበትን ምክንያት መግለጽ አለባቸው::

4) ሰብሳቢው በጉዳዩ ላይ በቂ ማብራሪያ አልሰጡም ብሎ የሚያምን ከሆነ፣ ባለሙያዎቹ ከሌላ አይታ አንጻር ጉዳዩን እንዲመለከቱት በመጠየቅ የሰጡትን አሳብ መከለስ ይኖርበታል::

5) ሰብሳቢው አስተያየታቸውን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት:: ብዙውን ጊዜ የባለ ጉዳዩ ቡድን ተወካይ በቦርዱ ላይ ተገኝቶ የሚነሡትን ጥያቄዎች እንዲመልስ ማድረጉ ጠቃሚ ነው:: ቦርዱ ውሳኔው ለምን እንዳስፈለገ፣ የውሳኔ አሳቡ ምን እንደ ሆነና ይህ የውሳኔ አሳብ ከሌሎች ይልቅ ለምን እንደ ተመረጠ በግልጽ መረዳታቸው አስፈላጊ ነው:: ቦርዱ በውሳኔው ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ ከመግባት ይልቅ፣ ምርጥ የሆነ ውሳኔ ለመስጠት ጥልቅ ምርመራ ማድረግ አለበት:: በውሳኔ አሳቡ (አስተያየቱ) እና አስተያየቱ በተሰጠበት ምክንያት ላይ ትልቅ ጥያቄ እስካልተነሣ ድረስ፣



ቦርዱ በተሰጠው የውሳኔ አስተያየት መስማማት አለበት:: ቦርዱ የውሳኔ አስተያየት አቅራቢዎች ያልዳሰሱትን ትልቅ ጉዳይ ካነሣ፣ ቦርዱ በዚህ መንገድ መለወጥ አለበት ከሚል አስተያየት ጋር ጉዳዩን ለአስተያየት አቅራቢው ቡድን ሊመልስና ሰብሳቢው ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ማድረግ ይኖርበታል::

> 3ኛ ጥያቄ:- የቀጣናው ቤተ ክርስቲያን ቦርድ ሰብሳቢ ነህ እንበል:: አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መከፈት አለበት የሚል አሳብ በአጀንዳነት መያዝ አለበት የሚል አሳብ አነሣ:: ይህ አጀንዳ በቦርዱ ፊት ቀርቦ ጥሩ ውሳኔ እንዲሰጥበት ምን ዓይነት ደረጃዎች መሟላት አለባቸው?

5. ሰብሳቢው ቦርዱ የሚወያይባቸውን ነገሮች በዝርዝር መያዝ አለበት:: ብዙውን ጊዜ የቦርዱ አባላት ካላቸው ጊዜ የበዛ አጀንዳ ይገጥማቸዋል:: በዚህም ምክንያት ጊዜው ያልቅና በአጀንዳነት የቀረቡት ነገሮች በሙሉ ቦርዱ ሳይወያይባቸው ይቀራሉ:: በአመዛኙ የቦርዱ አባላት ያን ያህል ስልታዊ አስፈላጊነት በሌላቸው ጉዳዮች ላይ ሲወያዩ ጊዜያቸውን ይጨርሱና ለቤተ ክርስቲያን የረዥም ጊዜ ጠቀሜታ ያላቸውን ነገሮች በጥድፊያ ወስነው ይለያያሉ:: እነዚህ ጉዳዮች በሚገባ ያልታሰበባቸው በመሆኑ፣ አንድም ውሳኔው ተፈጻሚነት አይኖረውም፣ ወይም አላስፈላጊ የሆኑ ክፍፍሎች ሊከሰቱ ይችላሉ:: ይህም የሚሆነው ውሳኔው የሚያስከትላቸው ነገሮች በሙሉ በሚገባ ያልተጤኑ በመሆናቸው ነው:: ወይም ደግሞ ቦርዱ ስልታዊ አስፈላጊነት ያላቸውንና አስቸኳይ አይደሉም የተባሉትን ጉዳዮች ውሳኔ ሳይሰጥ ያዘገያቸዋል:: ተወካዮቹ በሚዳከሙበት ጊዜ በግልጽ ለማሰብ አለመቻል ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸው መጣላትም ስለሚከጅላቸው፣ ቀደም ሲል የያዙትን አቋም ይዘው ይለያያሉ:: ብዙውን ጊዜ አስፈላጊ ውሳኔዎች የሚሰጡት መሪዎች በተዳከሙበት ሰዓት ወይም ጊዜ በሚያጥራቸው ወቅት ከሆነ፣ ሰዎች አቋማቸው ተደማጭነት ባለማግኘቱ ወይም በበቂ ሁኔታ ባለመታየቱ ምክንያት ያዝናሉ:: ምንም እንኳን የቦርዱ አባላት ወደ ቤታቸው ለመሄድ ቸኩለው ድምጽ ቢሰጡም፣ ለውሳኔው ልባቸውን አይሰጡም:: ለተግባራዊነቱም የሚችሉትን ሁሉ አያደርጉም:: ስለሆነም፣ መጀመሪ

ያውኑ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያስከትሉትን ጉዳዮች አንሥቶ መወያየቱ አስፈላጊ ይሆናል። ይህም ሲሆን የቦርዱ አባላት ከፍተኛ የማሰብ ብቃትና ውይይት የሚጠይቁትን ነገሮች ለማካሄድ ንቁ ሆነው ይሠራሉ።

አጀንዳው በሚከተሉት አራት ቅደም-ተከተሎች አኳያ መዘጋጀት አለበት።

<u>አንደኛ</u>፣ ከፍተኛ ስልታዊ አስፈላጊነት ያላቸው ነገሮች መጀመሪያ መጻፍ አለባቸው።

<u>ሁለተኛ</u>፣ ውስብስብና የሰዎችን አሳብ ለመከፋፈል የሚችሉ ጉዳዮች አሉ።

<u>ሦስተኛ</u>፣ አስፈላጊ የሆኑና ዳሩ ግን ለመወያየትና ለማጽደቅ ትንሽ ጊዜ ብቻ የሚበቃቸው ጉዳዮች ናቸው።

<u>አራተኛ</u>፣ ጊዜ ቢያጥር ለሌላ ጊዜ ሊተላለፉ የሚችሉ ውሳኔዎችም ይኖራሉ።

ሰብሳቢው የተለያዩ አጀንዳዎችን በሚያቀርብበት ጊዜ፣ ዝርዝሩን ከመከተል ይልቅ፣ ውይይቱን መምራትና ከግትርነት ይልቅ ተለማጭነትን ማሳየት ይገባዋል።

ሀ. በፍጥነት አልባት ሊሰጣቸው የሚችሉ አያሌ ትናንሽ ጉዳዮች ካሉ፣ ቦርዱ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ለማተኮር እንዲችል በፍጥነት ውይይት ተደርጎባቸው ሊጸድቁ ይገባል። ነገር ግን ትንንሾቹ ጉዳዮች ብዙ ጊዜ የሚፈልጉ ከሆነ፣ እነዚህ ጉዳዮች ወደ በኋላ መቅረብ ይኖርባቸዋል። በዚህ ጊዜ የተዳከሙት የቦርዱ አባላት እምብዛም ያልተወሳሰቡትን ጉዳዮች ለመወሰን አይቸገሩም። ወይም ደግሞ ለዋና ዋና ጉዳዮች መወያያ በቂ ጊዜ በማይኖርበት ሰዓት ላይ በእነዚህ አጀንዳዎች ላይ መወያየት ይቻላል። ለምሳሌ፣ የምሳ ሰዓት ከተቃረበ፣ በቀላሉ የማይቋጭ ከባድ ጉዳይ ከማንሣት ይልቅ፣ በፍጥነት ሊጠቃለል የሚችል ቀለል ያለ ጉዳይ ላይ መወያየቱ ተገቢ ይሆናል።

ለ. ዋና ዋናዎቹ ጉዳዮች ላይ ውይይት መካሄድ ያለበት አባላቱ ከመዳከማቸው በፊትና ለውይይቱ በቂ ጊዜ በሚኖርበት ጊዜ



መሆን አለበት። ስለሆነም፣ በጣም ስልታዊ ወይም በጣም አወዛጋቢ የሆኑ ጉዳዮች አባላቱ ከመዳከማቸው ቀደም ብለው በስብሰባው መጀመሪያ ላይ መቅረብ አለባቸው። እነዚህም ጥሩ ሰዓቶች ጠዋት፣ ከምሳ መልስ፣ ከሻይ መልስ፣ ወይም ከአራት ቀጥሎ ያሉት ሊሆኑ ይችላሉ።

ስብሰባው ለአንድ ቀን (ወይም ለጥቂት ሰዓታት) ብቻ የሚቆይ ከሆነ፣ ሰብሳቢው ከፍተኛ ስልታዊ ጠቀሜታ ባላቸውና ውሳኔ በሚጠይቁ ውይይቶች በመጀመር፣ ውስብስብ ጉዳዮችን ቢያስከትል መልካም ነው። ቀላሎቹን ጉዳዮች ለበኋላ ቢያቆያቸው፣ አባላቱ ቢዳከሙም እንኳን ብዙ መወያየት ሳያስፈልጋቸው ውሳኔ ሊሰጡ፣ ካልሆነም፣ አስተዳደሩ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ሊወስኑ ይችላሉ። የስብሰባው ጊዜያት በሚረዝሙበት ጊዜ ሰብሳቢው አጀንዳዎቹን ለማቅረብ የበለጠ ነጻነት ይኖረዋል። በዚህ ጊዜ ቀላልና ከባድ ጉዳዮችን እያለባጠሩ ማቅረቡ ጠቃሚ ነው። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያ መሪዎች በቀላል ጉዳዮች መጀመርን ይመርጣሉ። እነዚህ መሪዎች በጥንቃቄ ነገሮችን በመቆጣጠር ጥቂት ሰዎች ብቻ አስተ ያየት ከሰጡ በኋላ ወደ ድምጽ አሰጣጥ ያመራሉ። በጉዳዩ ላይ ብዙ የሚያወያዩ አሳቦች ከተነሡ፣ ጉዳዩን ለበኋላ ያቆዩታል። በዚህ ዓይነት ብዙ ጉዳዮችን ለበኋላ በሚያቆዩበት ጊዜ የቦርድ አባላቱ ብዙ ሥራ ሠርተናል ብለው ያስባሉ። በተጨማሪም አሳባቸውን ከቀላል ጉዳዮች አንሥተው በወሳኝ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ይችላሉ።

ስብሰባው ለብዙ ቀናት የሚቆይ ከሆነ፣ አጅግ ስልታዊና አስቸጋሪ የሆኑትን ጉዳዮች ሰዎች ንቁ በሆኑበት በጠዋቱ ክፍለ ጊዜ መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል። እምብዛም ከባድና አነስተኛ ስልታዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ጉዳዮች ደግሞ ደከም በሚሉባቸው የከሰዓት በኋላ ክፍለ ጊዜያት መወያየቱ ጠቃሚ ይሆናል። የስብሰባው ዓላማ የቀረቡትን አጀንዳዎች ነካክቶ መጨረስ ሳይሆን፣ በተቻለ መጠን ምርጥ ውሳኔ መስጠት መሆን አለበት።

ስብሰባዎችን ስለ ማዘጋጀትና በጠቃሚ ጉዳዮች ላይ ከስምምነት ስለ መድረስ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የሚከተለውን አሳብ ሰንዝሯል።

ሀ. ከስብሰባዎቹ 80 በመቶውን ቤተ ክርስቲያኒቱን ስለሚመሩት ስልታዊና አስፈላጊ ነገሮች አስቡ። ከስብሰባው 20 በመቶውን ቀድሞውኑ ስምምነት ላይ የተደረሱትን ነገሮች በማጠናቀቅ ላይ አውሉት።

ለ. አስፈላጊ ወይም ከፋፋይ ጉዳዮችን ወደ ድምጽ አሰጣጥ ለመውሰድ ከመጣደፍ ይልቅ፣ በአያሌ ስብሰባዎች ላይ ስለ ጉዳዩ በሚገባ መወያየቱ የተሻለ ነው። በመጀመሪያው ሰብሰባ ላይ ጉዳዩን ማስተዋወቁ ጠቃሚ ነው። ይህንንም የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄ ዎች በማንሣት መጀመር ይቻላል። «ከዚህ ነገር ምን ዓይነት ጥሩ ነገር ሊገኝ ይችላል? ምን ዓይነት ችግሮች አሉት? የዚህ አሳብ ጠቃሚና ጎጂ ገጽታዎች ምን ምንድን ናቸው?» ውሳኔ እንዲሰጡ ስላልተጠየቁ፣ ሰዎች ለእንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ግልጽ የሆነ አሳብ ሊያካፍሉ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ መሪው ሰዎቹ አዲሱን አሳብ መደገፍ አለመደገፋቸውን ሊገነዘብ ይችላል። በቀጣይ አያሌ ወርሐዊ ስብሰባዎች ላይ መሪው አሳቡን በማወያየት ሁሉም ወደ ስምምነት የሚደርሱበትን መንገድ ያመቻቻል። ድምጽ እንዲሰጡ ማድረግ ያለበት ሁሉም አንደ ተስማሙበት ሲያውቅ ብቻ መሆን አለበት።

ሐ. መሪው በቦርዱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ማንነት ማወቅ አለበት። አንዳንዶቹ ፈጣን ውሳኔ-ሰጭዎች ሲሆኑ፣ ሌሎች ደግሞ አሳባቸውን የሚያቀርቡት ዘግየት ብለው ነው። ጥድፊያ መፍጠሩ ቀስ ብለው የሚያስቡትን ሰዎች አሳብ ከጨዋታ ውጭ ያደርገዋል። የቤተ ክርስቲያን መሪው በእያንዳንዱ ሰው አእምሮ ውስጥ ያለውንና አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያስበውን ነገር ማወቅ አለበት። መሪው የቦርድ አባላትን በቅርበት በሚያውቅበት ጊዜ፣ እያንዳንዳቸው ለአንድ ጉዳይ የሚራቸውን አመለካከትና ተቀባይነት ለማግኘት በምን መንገድ ጉዳዩን ማቅረብ እንዳለበት አስቀድሞ ያውቃል። የቡድኑ አባላት መሪዎች እንደ መሆናቸው መጠን፣ በቀዳሚነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ መሻት እንዳለባቸው ሊያስገነዝባቸው ይገባል። የቦርዱ ጥረት ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚሻለውን ነገር ማድረግ ነው። የቦርዱ አባላት ከሁሉም የተሻለ ውሳኔ ለመስጠት አብረው እንዲሠሩ ሊያግዛቸው ይገባል። ሰዎች በነጻነት እንዲናገሩ፣ የግል ወይም የአካባቢ አጀንዳቸውን ትተው በጋራ እንዲሠሩ የሚያደርገው እንዲህ ዓይነቱ መንፈስ ነው።



መ. መሪው ልቡን በጥንቃቄ በመጠበቅ እነዚህን ሁለት ነገሮች ማረጋገጥ ለአበት። 1) ለቦርዱ ያቀረበው ጉዳይ ለራሱ አንዳች ጥቅም ለማግኘት ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚሻለውን በመሻት መሆኑን፣ እና 2) በቡድኑ ውስጥ ያሉት ሁሉ በሁኔታው ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ማወቃቸውን ለማረጋገጥ ራሱን ዝቅ አድርጎ እያንዳንዱ የቦርዱ አባል የሚናገረውን አሳብ መስማት አለበት። ሰዎች አሳቡን አክርረው በሚቃወሙበት ጊዜ ሳይቀር ራሱን ከንዴትና ከመራርነት መጠበቅ አለበት። ይልቁንም፣ ሰዎች በሚቃወሙት ጊዜ፣ በዚህ የተቃውሞ አሳብ ውስጥ አንዳች ጥበብ ይኖር ይሆን? በማለት በጽሞና መስማት ይገባዋል። እግዚአብሔር በራሱ መንገድና ጊዜ በጉዳዩ ላይ የሰዎችን አሳብ እንዲያስማማ ለአርሱ አሳልፎ መስጠቱ ጠቃሚ ነው። ሥራው የእግዚአብሔር ከሆነ፣ የሰዎችን አሳብ መቀየር ያለበት መንፈስ ቅዱስ እንጂ እርሱ አይደለም።

ሠ. የቤተ ክርስቲያን መሪው ሁሉንም አሳብ ራሱ ከሚያቀርብ ይልቅ፣ ሌሎች መሪዎችም የየራሳቸውን አሳቦች እንዲሰጡ ማድረግ ይኖርበታል። አሳቦቻቸውን በጥሩ ምክንያቶች እንዲያስደግፉ ሊጠይቃቸውና ለመልካም አስተሳሰባቸው ሊያመሰግናቸው ይገባል። ወይም ደግሞ አሳቡ የመነጨው ከሌላ ሽማግሌ ወይም ሠራተኛ ከሆነ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ግለሰቡ አሳቡን ለቡድኑ እንዲያቀርብ ማድረግ ይገባዋል። ይህ የቡድኑ አባላት መሪው የራሱን አሳብ እንደማይጭንባቸውና ለቡድኑ ከሁሉም የተሻሉትን አሳቦች ለማቅረብ እየፈለገ መሆኑን ያሳያል።

ረ. ብዙውን ጊዜ በቡድኑ ውስጥ ሰዎች የእነርሱን እሳብ እንዲቀበሉ «ተጽዕኖ የማሳደር» ብቃት ያላቸው ሰዎች አሉ:: እንዳንድ ጊዜ እነዚህ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን መሪውን የሚቃረን እቋም ሊይዙ ይችላሉ:: በዚህ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪው ከእነዚህ ሰዎች ጋር ጊዜ በመውሰድ ለምን የእርስን አሳብ እንደሚቃወሙ መረዳት አለበት:: ከዚያም መሪው ለእነዚህ ተጽዕኖ የማሳደር ብቃት ላላቸው ሰዎች አሳቡን በግልጽ ማብራራት ይኖርበታል:: በአመዛኙ እነዚህ ተደማጭነት ያላቸው ሰዎች ከተ ስማሙ፣ የተቀሩት የቦርዱ አባላት አሳቡን ይደግፋሉ::

ሰ. መሪው በቦርዱ አባላት መካከል በአመኔታ ላይ የተመሠ ረተ ግንኙነት እንዲመሠረት መጣር አለበት:: በተወካዮች መካከል አለመስማማቶች ካሉ፣ እንድን ጉዳይ አስመልክቶ ከስምምነት መድ ረሱ እስቸጋሪ ይሆናል:: ከዚህ ይልቅ፣ ጸበኞቹ ቡድኖች ተቃራኒ እቋሞችን ስለሚይዙ፣ የእንደኛውን ወገን አቋም የሚደግፍ ውሳኔ በሌላኛው ቡድን ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም:: የቤተ ክርስቲያን መሪው በተጨማሪም ሰዎች ጉዳዮችን መመልከት ያለባቸው ለአገልግሎት ዘርፋቸው ወይም ለቀጣናቸው በሚያስገኘው ጥቅም ላይ በመመሥረት ሳይሆን፣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር መንግሥት ይጠቅማል ወይ? ከሚል ሰፊ እይታ አንጻር መሆን እንዳለበት ሊያስገነዝባቸው ይገባል:: የቤተ ክርስቲያን መሪው ውሳኔው በሌ ሎች አካባቢዎች ላይ የሚያስከትለውን ውጤት በማሳየት፣ ሁሉም ጉዳዩን ከሌሎች አይታ አንጻር እንዲመለከቱ ሊያነሣሣቸው ይችላል::

4ኛ ጥያቄ:- . ሀ) በቦርድ ወይም በኮሚቴ ውስጥ ተሳትፈህ የምታውቅ ከሆነ፣ ከተነሡት አጀንዳዎች አንዳንዶቹን ጥቀስ:: ለ) ስልታዊ ጠቀሜታ የነበራቸው አጀንዳዎች የትኞቹ ነበሩ? ሐ) ውስብስብ የነበሩት አጀንዳዎች የትኞቹ ነበሩ? መ) ቀላሎቹስ? ሠ) ቦርዱ ከቀላልና እምብዛም ጥቅም ከሌላቸው ይልቅ ስልታዊ ጠቀሜታ ባላቸውና ውስብስብ በሆኑት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ለማድረግ እንዲችል አጀንዳዎቹ እንዴት ባለ ቅደም-ተከተል ቢቀርቡ ይሻል ነበር? ረ) ስብሰባው አስፈላጊ ካልሆኑት ጉዳዮች ይልቅ ጠቃሚ በሆኑት ላይ ትኩረት ለማድረግ እንዲችል ምን ቢደረግ መልካም ነው?



5ኛ ጥያቄ:- ሀ) ይህንን የውሳኔ-ሰጭነት ዘዴ ብንከተል፣ አብዛኞቹ የሽማግሌዎችና የቦርድ ስብሰባዎች እንዴት የሚቀየሩ ይመስልሃል? ለ) ከዚህ ዓይነቱ የስብሰባ አካሄድ ምን ዓይነት ጥቅሞችን ታያለህ? ሐ) ስብሰባዎችን በዚህ መንገድ ማካሄድ የሚያስከትላቸው ችግሮች ምን ምንድን ናቸው? መ) በቦርድ ስብሰባዎች ላይ የሚሰጡትን ውሳኔዎች ጥራት ለማሻሻል ምን ቢደረግ መልካም ነው?

6. ውስብስብ በሆኑት ጉዳዮች ላይ በመወያየት ላይ የሚባክነው የቦርድ ስብሰባዎች ጊዜ ቀላል አይደለም:: ብዙውን ጊዜ የቦርዱ አባላት በጉዳዩ ላይ በቅጡ ለማሰብ ጊዜ ያጥራቸዋል:: ስለ ጉዳዩ ለማሰብና ለመጸለይ በቂ ጊዜ ከሌላቸው፣ የቦርዱ አባላት ለአንድ ውስብስብ ጉዳይ አጥጋቢ ውሳኔ ሊሰጡ አይችሉም:: የመወያያ እሳቡ ውስብስብ ከሆነ፣ ከሚከተሉት ሁለት ነገሮች እንዱን ማድረግ ተገቢ ይሆናል::

ሀ. ስብሰባው ከመጀመሩ ከብዙ ሳምንታት በፊት ለእያንዳንዱ የቦርድ እባል ስለ ጉዳዩ የሚገልጽ ጽሑፍ ማስተ ላለፍና እያንዳንዱ እባል የተሰጠውን ጽሑፍ አንብቦ፣ ጸልዮበትና አስቦበት እንዲመጣ መጠየቅ:: በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሚከተሉት ዓይነት ነገሮች መስፈር አለባቸው:- 1) ታሪካዊ ሥረ-መሠረትና ውሳኔው ለምን አንዳስፈለገ ማብራራት፣ 2) የተለያዩ አማራጭ ውሳኔዎች፣ 3) አስተዳደሩ ምርጥ ውሳኔ ነው ብሎ የሚያስበው አሳብ፡ 4) ውሳኔው ጠቃሚ ነው ተብሎ የሚታመንበት ምክንያት፣ 5) የውሳኔው አዎንታዊ እስከትሎቶች፣ እና 6) የውሳኔው አሉታዊ እስከትሎቶች:: አባላቱ ይህን መረጃ ከስብሰባው በፊት ካገኙ፣ በስብሰባው ላይ ውሳኔውን ለመረዳት የሚያጠፉት ጊዜ ስለሚቀንስ፣ ስለ ውሳኔው ለመወያየት በቂ ጊዜ ይኖራቸዋል:: እሳቡን ካነበቡና ከጸለዩበት በኋላ፣ እባላቱ ወደ ስብሰባው የሚመጡት በሰነዱ ላይ ለመወያየት ይሆናል:: ይህም አባላቱ በጉዳዩ ላይ በጥልቀት በማሰብና የቀረበውን አስተያየት በማመዛዘን አስፈላጊ ናቸው የሚሏቸውን የለውጥ አሳቦች እንዲያካትቱ ያስችላቸዋል::

ለ. ቦርዱ ውስብስብና ዳሩ ግን አጣዳፊ ያልሆኑትን ጉዳዮች በእያሌ ተከታታይ ስብሰባዎች ሊያስተናግድ ይችላል:: በመጀመሪያው ስብሰባ ላይ፣ ሰብሳቢው ሰነዱን እንዲያስቡበት ያቀርብላቸዋል:: በዚህም ጊዜ የሰነዱን ዐበይት ነጥቦችና የአገልግሎቱ ተሳታፊዎች ያቀረቧቸውን አስተያየቶች ሊናገር ይችላል:: የቦርዱ አባላት በሰነዱ ውስጥ ያልተካተተ አዲስ አሳብ እንዳላቸው ለመመልከት ለአጭር ጊዜ እንዲወያዩበት ሊያደርግ ይችላል:: ከዚያም አባላቱ ሰነዱን ወደ ቤታቸው በመውሰድ እንዲያስቡበት፣ እንዲጸልዩበትና ለሚቀጥለው ስብሰባ አስተያየቶቻቸውን ይዘው እንዲመጡ መጠየቁ ተገቢ ይሆናል::

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ ዘለቄታዊ ለውጥ በሚያስከትሉ ዐበይት አጀንዳዎች ላይ ሁሉም የቦርድ አባላት ከስምምነት እንዲደርሱ ይፈልጋሉ:: በመሆኑም፣ ሰብሳቢው የቦርዱ አባላት ድምጽ እንዲሰጡ ከመጠየቁ በፊት ጉዳዩን በብዙ የቦርድ ስብሰባዎች ላይ በማወያየት ከስምምነት ላይ እንዲደርሱ ይጥራል:: አንዳንድ የቦርድ አባላት ይህን አሳብ አልወደዱትም የሚል ግምት ካለው፣ ከእነዚህ ሰዎች ጋር በግል ደረጃ በመወያየት አመለካከታቸውን ለመረዳት ይጥራል፤ የራሱንም አሳብ ያጋራቸዋል:: ሁሉም ሰው በአሳቡ እንደ ተስማማ በሚገነዘብበት ጊዜ፣ ድምጽ እንዲሰጥበት ያደርጋል:: አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን መንገድ የሚከተሉት ለሁለት ምክንያቶች ነው:- በ<u>መጀመሪያ</u>፣ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሳቡ የመንፈስ ቅዱስ ከሆነና ሁሉም ሰው መንፈሳዊና የእግዚአብሔርን መንግሥት መስፋፋት የሚፈልግ ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ የቦርድ አባላቱን አሳብ ወደ አንድነት ያመጣዋል ብለው ያምናሉ:: <u>ሁለተኛ</u>፣ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ መሪዎቹ የአሳብ አንድነት ከሌላቸው፣ በድምጽ ብልጫው የሚሸነፉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የአብዛኛዎቹን ውሳኔ አይደግፉም:: ሰይጣንም ይህንን የአሳብ ልዩነት በመጠቀም ክፍፍልን ያባብሳል:: በመሆኑም፣ በኋላ አለመስማማትን የሚያመጣ ውሳኔ በጥድፊያ ከመወሰን ይልቅ፣ የሰዎች የአሳብ አንድነት እስኪገኝ ድረስ መቆየቱ የተሻለ ይሆናል::



የቤተ ክርስቲያን መሪው መረጃውን በጽሑፍ ለተሳታፊዎቹ ለማዳረስ ካልቻለ፣ በሁሉም አጀንዳዎች መጀመሪያ ላይ የጉዳዩን ታሪካዊ አመጣጥ (ቀደም ሲል ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተሰጡ ውሳኔዎች ካሉ ጭምር)፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ሊሰጡ የሚችሉትን የተለያዩ ውሳኔዎች ከአዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎቻቸው ጋር፣ እንዲሁም አስተዳደሩ (ወይም አስፈጻሚው ኮሚቴ) ጉዳዩ በምን መንገድ እልባት ቢያገኝ ይሻላል ብሎ እንደሚያምን ለቦርዱ አባላት ማብራራት አለበት:: ሰብሳቢው ይህንን የሚያደርገው የቦርዱ አባላት ከአስተዳደሩ አሳብ ጋር እንዲስማሙ ለማስገደድ ሳይሆን፣ ሰዎቹ ስለ ጉዳዩ ግንዛቤ አግኝተው የተሻለ ውሳኔ ለመስጠት እንዲችሉ ለማገዝ ነው:: አባላቱ ምንንም ስለማያውቁት ጉዳይ ውሳኔ እንዲሰጡ መጠየቅ ጊዜ ማባከኑ የማይቀር ነው:: ለዚህም ምክንያቱ ሰዎቹ መረጃዎችን ለማግኘት ወይም ስለ ጉዳዩ በሚገባ ለማሰብ ስለሚፈልጉ ነው::

7. የቦርድ ስብሰባ ቀዳሚ ዓላማ ለቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ መወሰን ስለሆነ፣ ቦርዱ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናትና በዚህ ጉዳይ ላይ ፈቃዱ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ጊዜ መውሰድ አለበት:: የራሳችንን ውሳኔ ለመስጠት መጣደፍ የለብንም:: ምክንያቱም ይህንን ካደረግን፣ የሚኖረን የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሳይሆን፣ የራሳችን ጥበብ ብቻ ነው:: የቤተ ክርስቲያን ቦርዶች ጥሪት የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ እንዲያከናውኑ የሚፈልገውን ነገር ማድረግ ነው:: በመሆኑም፣ እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ የገለጠውን ፈቃዱን ለማወቅ መጣር አለባቸው:: መንፈስ ቅዱስ በልባቸው የሚናገረውንም ነገር መስማት ይኖርባቸዋል:: መሪዎች በሁሉም ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ፈቃዱ የሌለበትን የተሳሳተ ውሳኔ ከመስጠት እንዲያስቆማቸው መጠየቅ ይኖርባቸዋል:: «ጌታ ሆይ፣ እርዳን፣» ከሚሉ ዓይነት አጠቃላይ ጸሎቶች ይልቅ፣ በአጀንዳው ላይ ባሉት በእያንዳንዳቸው ጉዳዮች ላይ መጸለዩ የተሻለ ነው:: አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ በቅደም-ተከተል መጸለዩ ጠቃሚ እንደ ሆነ ተገንዝበዋል:: በጉዳዩ ላይ ሰዎች ለመስማማት በሚቸገሩበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪ

ዎች ውሳኔ ለመስጠት ከመጣር ይልቅ፣ ቆም ብለው መጸለይ ይገባቸዋል። ይህ በውሳኔው ላይ የእግዚአብሔርን ርዳታ ከማምጣቱም በላይ፣ እግዚአብሔር ጸሎቱን በመጠቀም ከራሳችን የራስ ወዳድነት መንግሥታት በላይ የእግዚአብሔርን መንግሥት መሻት እንዳለብን ያስረዳናል (ማቴ. 6:33)።

8. መሪዎች ከጋራ ስምምነት ላይ ለመድረስ አብረው በሚሠሩበት ጊዜ፣ «የሌላውን ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ እያስገቡ የማዳመጥን» ክህሎት ማሳደግ አለባቸው። (ትምህርት 14ን ተመልከት።) ጥራት ያላቸውን ውሳኔዎች መስጠት የሚቻለው ለዎች እርስ በርሳቸው ሲደማመጡና በነጻነት አሳባቸውን ሊያካፍሉ ብቻ ነው። ይህ ካልሆነ፣ ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ኩራትና ራስ-ወዳድነት በመጠቀም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እንዲጋጩ ሊያደርግ ይችላል። በዋናነት አንድ ስብሰባ ፍሬያማ የሚሆነው ወይም የማይሆነው ሰብሳቢው ነገሮችን ከሚይዝበት ሁኔታ አንጻር ነው። አንድ መሪ እንደ ተናገረው፣ «መሪዎች ጥሩ ያልሆኑትን ስብሰባዎች የሚያካሂዱት ከሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት ባለማድረጋቸው ምክንያት ነው።» ስብሰባዎች ፍሬያማ የሚሆኑት ወይም የማይሆኑት መሪዎች ከሰዎች ጋር እንዴት መሥራት እንዳለባቸው፣ ብሎም እግዚአብሔርን ሰምተው እንዴት የአስተዋይነት ውሳኔ ሊወስኑ እንደሚችሉ ተጽዕኖ ለማሳደር በመቻላቸው ወይም ባለመቻላቸው ነው።

9. ሰብሳቢው አጀንዳውን በሚያስተዋውቅበት ጊዜ፣ ያለውን መረጃ፣ ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ታሪካዊ ውሳኔዎች፣ መፍትሔ ለማምጣት የተወሰዱትን እርምጃዎችና ጉዳዩን በተመለከተ የሚገነዘባቸውን አሉታዊና አዎንታዊ ገጽታዎች በአጭሩ መግለጽ አለበት። የቦርዱ አባላት በመረጃው ሥረ-መሠረት ላይ ጥያቄዎች ካሏቸው እንዲያነሡ መጠየቅ አለበት። ይህ ሁሉም መሪዎች ለውይይት የቀረበውን ጉዳይ እንዲያውቁና ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል መረጃ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ከዚያም ውሳኔ የሚሰጥበትን ጉዳይ ገልጾ ማብቃት አለበት። መሪዎቹ ውሳኔ የሚሰጠው በምን ጉዳይ ላይ እንደ ሆነ ካላወቁ፣ አላስፈላጊ



አሳብ ወይም መረጃ እያነሡ ብዙ ጊዜ ሊያጠፉ ይችላሉ። ነገር ግን ውሳኔ የሚጠይቀው ጉዳይ ግልጽ በሚሆንበት ጊዜ፣ ውሳኔው ግልጽና የተሻለ ይሆናል።

10. እያንዳንዱ ሰው መፍትሔ ለመስጠት ሲሞክር፣ ብዙ ጊዜ የሚወስዱ ጉዳዮች በሚኖሩበት ጊዜ፣ መሪው ጥቂት የቦርዱ አባላት የሚገኙበትን ንዑስ ኮሚቴ በመመሥረት በጉዳዩ ላይ ተወያይተው የውሳኔ አሳብ እንዲያመጡ ቢያደርግ የተሻለ ይሆናል። ይህ ብዙውን ጊዜ በሁለት መንገዶች እገዛ ያደርጋል። አንደኛ፣ ብዙ ጊዜ ያድናል። የቦርዱ አባላት ሁሉ በአንድ ጉዳይ ላይ አሳባቸውን ለመስጠት በሚሞክሩበት ጊዜ የሚባክነው ሰዓት፣ ሦስት ወይም አራት ሰዎች በሚወያዩበት ጊዜ ከሚባክነው ያነሰ ነው። ሁለተኛ፣ ይህ ጉዳዩን በጥልቀት ለመመርመር ስለሚያስችል፣ የተሻለ መፍትሔ ያስገኛል።

11. አንዳንድ መሪዎች እያንዳንዱ የቦርዱ አባል የራሱን አሳብና የሚያሳስቡትን ነገሮች እንዲገልጽ አጭር ጊዜ ሊሰጡ ይችላሉ። ከዚያም ንዑስ ኮሚቴ በጉዳዩ ላይ በመወያየት የውሳኔ አሳብ ይዞ ወደ ቦርዱ እንዲመለስ ይጠይቃሉ። ይህ ቦርዱ በውስብስብ ጉዳይ ላይ ከመወያየት ይልቅ የንዑስ ኮሚቴውን የውሳኔ አሳብ በማስተካከል በቀላሉ አልባት እንዲሰጥ ያስችለዋል።

የቤተ ክርስቲያን መሪው ተወካዮቹ በጠንካራ ስሜት የሚገልጹአቸው የተለያዩ አቋሞች በሚኖሩበት ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአብዛኛውን አባላት የድምጽ ድጋፍ ለማግኘት በመሻት የራሳቸውን አቋም በትጋት ያንጸባርቃሉ። በኋላ አሳባቸው ተቀባይነት ያላገኘላቸው ሰዎች ስሜታቸው ስለሚጎዳ ከውሳኔው ጋር አይተባበሩም። ወደፊትም አንድ አስፈላጊ ውሳኔ በሚኖርበት ጊዜ፣ መሪውን ወይም አሳቡ «ያሸነፈለትን» ተወካይ ለመቃወም ተዘጋጅተው ይመጣሉ። ሁሉም ሰው ከስምምነት ላይ እንዲደርስ የምንችለውን ጥረት ሁሉ አድርገን ሳይሳካልን በመቅረቱ በድምጽ ብልጫ ለመወሰን የምንገደድበት ጊዜ ሊኖር ይችላል። ይሁን እንጂ፣ ሰብሳቢው የሁሉንም ሰው ድጋፍ ለማግኘት መጣር አለበት።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መንፈስ ቅዱስ ቦርዱን በትክክል እየመራው ከሆነና ሁሉም ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያስብ ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ የቦርዱን አባላት ልብና አሳብ ወደ አንድነት ያመጣል ብለው ያምናሉ:: ይህንን መንፈስ ቅዱስ ተሰብሳቢዎቹ ሁሉ አሕዛብ እንዲገረዙ አንጠይቅም ከሚል ስምምነት እንዲደርሱ ከመራበት ሁኔታ ልንመለከት እንችላለን (የሐዋ. 15:28)::

6ኛ ጥያቄ:- ሀ) የሰዎችን ስሜት የጎዳና በሽማግሌዎች መካከል ክፍፍልን የፈጠረ ውሳኔ በአብዛኛው ድምጽ ሲወሰን የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) በውሳኔው ያልተስማሙ ሰዎች በአካባቢያቸው በአብላጫ ድምጽ የተወሰነውን ጉዳይ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ያላደረጉት እንዴት ነው?

12. መሪዎች የትኛውም አንድ ግለሰብ ስብሰባዎችን ሳይቆጣጠር ሁሉም ተሳታፊዎች በእኩል ደረጃ አሳባቸውን እንዲገልጹ ማድረግ አለባቸው:: ተወካዮቹ ሌሎች አመለካከታቸውን እንዳዳመጡ በሚገነዘቡበት ጊዜ፣ የሌሎችን አሳብ ለመስማት ፈቃደኞች ይሆናሉ:: በተሰጠው አሳብ ባይስማሙ እንኳን፣ አሳባቸው መደመጡን ካወቁ ውሳኔውን ለመቀበል ፈቃደኞች ይሆናሉ:: ብዙው ጊዜ በጣም ተናጋሪ የሆኑ ጥቂት ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: በዚህ ጊዜ መሪው ጠንቃቃ ካልሆነ፣ እነርሱ ብቻ ሙሉውን የስብሰባ ጊዜ ተናግረው ሌሎች የማይደግፉትን አሳብ ለማጽደቅ ጥረት ሊያደርጉ ይችላሉ:: ሌሎች፣ በተለይም ከገጠር አካባቢ የሚመጡ አንዳንድ ሰዎች፣ አሳባቸውን ለመግለጽ ፈቃደኞች ላይሆኑ ይችላሉ:: አስተዋይ መሪ እነዚህ ዝምተኛ ሰዎች አሳባቸውን እንዲገልጹ ያበረታታቸዋል:: በአመዛኙ ሰዎች ከውሳኔ ሰጭነቱ ሂደት አንድንገለል ተደርጓል የሚል ግምት ካላቸው፣ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ማሰማታቸው የማይቀር ነው:: ሌሎች አሳባችንን ሰምተዋል የሚል እምነት ባይኖራቸውም፣ ዝምተኞቹ መሪዎች በውሳኔው ላይ ተቃውሞ ላያሰሙ ይችላሉ:: ነገር ግን ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚወስዱት እርምጃ አይኖርም::



13. የገጠርና የከተማ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተሰባጥረው በሚገኙበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪው ሰዎች በስብሰባዎች ላይ የሚሳተፉባቸውን ሁለት የተለያዩ መንገዶች ለማመጣጠን መጣር ይኖርበታል:: የገጠር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉም ሰው በስብሰባው ላይ አሳቡን እንዲናገር ይፈልጋሉ:: አንድ ሰው ያሰበውን ነገር ሌላው ቀደም ብሎ ቢናገር እንኳን ደግሞ እንዲናገር ይደረጋል:: የገጠር ሰዎች በጉዳዩ ላይ ከስምምነት ላይ ደርሰናል ብለው የሚያስቡት በአብላጫ ድምጽ ሳይሆን፣ የአሳብ ድግግሞሽ ሲበዛ ነው:: የተማሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ደግሞ አንድ ሰው ለውሳኔው የሚያክለው አዲስ ነገር ብቻ እንደሚናገር የሚያውቁ ሲሆኑ፣ ጉዳዩንም የሚቋጩት በአብላጫ ድምጽ ነው:: ሁለቱም ዓይነት መሪዎች በሚኖሩበት ጊዜ፣ በአብዛኛው እነዚህ ሁለት የአሠራር ሂደቶች ይጋጫሉ:: ሁሉም ተደማጭነት አግኝተናል ብለው እንዲያስቡ አስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሁለቱንም የስብሰባ አካሄዶች ለማክበር ይሞክራል:: ይህንንም በሚያደርግበት ጊዜ፣ የጊዜ እጥረት መኖሩንና እያንዳንዱ ሰው አዳዲስ አሳቦችን በአጭር በአጭሩ ብቻ የሚናገርበትን ዘዴ በብልሃት ያስተምራል::

14. ብዙውን ጊዜ የሰውጥ አሳብ ይዞ ከመምጣት ይልቅ ሰዎችን መተቸቱ ቀላል ነው:: ስለሆነም አንድን አሳብ የሚቃወሙ የቦርድ አባላት አማራጭ መፍትሔዎችን ማቅረብ እንዳለባቸው ማሳሰቡ ጠቃሚ ነው::

15. የቦርድ አባላት እጅግ ምርጥ ውሳኔዎችን እንዳይሰጡ ችሎታቸውን የሚገድቡትን ነገሮች በመወያየት ጊዜያቸውን እንዳያጠፉ ለብላቢው ጥንቃቄ ማድረግ አለበት:: ብዙውን ጊዜ መሪዎች የሚመጡት ከሩቅ ስፍራዎች ተጉዘው ነው:: በቤታቸውና በአካባቢያቸውም የሚፈጽሟቸው ተግባራትና ኃላፊነቶች አሏቸው:: ስለሆነም፣ በስብሰባው ላይ ለረዥም ጊዜ ሊቆዩ አይችሉም:: ይህም ሆኖ፣ በጣም ጠቃሚ ውሳኔዎችን መስጠት ይጠበቅባቸዋል:: የመሪዎች ጊዜ በጣም ውድና ውስን በመሆኑ፣ በቡድን ስብሰባዎች ላይ ጊዜያቸውን በጥበብ መጠቀም አለባቸው:: ይህም ማለት አስፈላጊ በሆኑት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግና አስፈላጊ ያልሆኑት ላይ

ጊዜ እለማጥፋት ማለት ነው:: በተጨማሪም፣ ጊዜ እናባክንም ማለት ነው:: በአመዛኙ ጊዜ የሚባክነው በአራት መንገዶች ነው::

ሀ. <u>በስብሰባ ቦታዎች ላይ በሰዓቱ ባለመድረስ</u>:: ብዙውን ጊዜ ተወካዮች ለቦርድ ስብሰባዎች ልክ በተባለው ሰዓት እይደርሱም:: የሻይ ወይም የምሳ ዕረፍት በሚሆንበት ጊዜም እንዲሁ ልክ በሰዓቱ ወደ ሰብሰባው ቦታ አይመለሱም:: አንዳንዶች ልክ በሰዓቱ ሲደርሱ፣ ሌሎች ግን አይደርሱም:: ሁሉም መሪዎች ካልደረሱ ደግሞ ስብሰባው እይጀመርም:: በሰዓቱ የደረሱት ያረፈዱትን በመጠበቅ ውድ ጊዜያቸውን ያባክናሉ:: ተወካዮች ልክ በሰዓቱ ስብሰባ ላይ እለመገኘታቸው የሌሎችን ጊዜ የሚያባክንና ለሌሎች አክብሮት አለመስጠታቸውን የሚያሳይ ነው:: በተጨማሪም፣ ይህ ለእግዚአብሔር ሥራ ግድየለሽ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው:: እንድ መሪ ወደ ስብሰባ አርፍዶ መምጣቱ፣ መሪዎቹ በአስፈላጊ ጉዳዮች ላይ የሚወያዩበትን ጊዜ ይቀንሰዋል:: ስብሰባዎችን በጊዜ ለመጀመር ግድየለሾች መሆናችንን በመጠቀም ሰይጣን ጥሩ ውይይቶችን ከማካሄድና ውሳኔዎችን ከመስጠት እንዳይከለክለን መጠንቀቅ እለብን:: እያንዳንዱ ተወካይ በጊዜ ለመድረስና ለግል ወይም ከቦርዱ ጋር ሳልተያያዙት ጉዳዮች ከክፍሉ ሳለመውጣት ቁርጥ ውሳኔ ማድረግ እለበት:: ሁሉም መሪዎች ሰብሳቢው ወይም ሌሎች መሪዎች በመቅረታቸው እነርሱን በመጠበቅ የሚያባክኑትን ጊዜ አስብ:: እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ጊዜ የሚያባክኑትን ሰዎች በኃላፊነት እንደሚጠይቃቸው የሚያጠራጥር አይደለም::

በተጨማሪም፣ ሰዎች ወደ ስብሰባው ክፍል ከገቡ በኋላ የግል ወይም የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮቻቸውን ለመፈጸም ገባ ወጣ በማለትም ጊዜ ያባክናሉ:: ሰዎች ከስብሰባው ስፍራ በሚወጡበት ጊዜ እያሌ ነገሮች ይከሰታሉ:- 1) ግለሰቡ በሚወጣበት ጊዜ ንግግር የሚያደርገው ግለሰብ ስሜት ይጎዳል:: ምክንያቱም እርሱ እየተናገረ መውጣቱ የእርሱ ንግግር ለእኔ እርባና የለውም የሚል መልእክት ያስተላልፋል:: 2) አንዳንድ ጊዜ የቦርዱ እባላት ድምጽ ስለማይሰጡ፣ ውሳኔ መስጠት ሳይቻል ይቀራል:: 3) የቦርዱ



አባላት በውይይቱ ላይ ባለመገኘታቸው፣ የውሳኔውን አሳብ አይቀበሉም:: 4) ተመልሰው ከመጡ ደግሞ ሌሎች ተነጋግረው ስለ ጨረሱት ጉዳይ ጥያቄ ያነሣሉ:: ይህም በበኩሉ የስብሰባውን ጊዜ ያባክናል::

ተወካዮች የስብሰባ ጊዜን ከሚያባክኑባቸው መንገዶች አንዱ ሞባይላቸውን (ተንቀሳቃሽ ስልካቸውን) ባለማጥፋት ነው፤ ሞባይላቸውን በማያጠፉበት ጊዜ ሰዎች ይደውሉላቸዋል:: በዚህ ጊዜ የቦርዱ እባላት ውይይቱን በማዳመጥ ፈንታ ስልክ የደወለላቸውን ሰው ያዳምጣሉ:: እንዳንድ ጊዜ ግለሰቡ የስልክ ንግግሩን እስኪጨርስ ድረስ ሌሎች ቆመው ይጠብቁታል:: ይህ እንዳይሆን በስብሰባ ጊዜ ተሰብሳቢዎች ሞባይሎቻቸውን ማጥፋት እለባቸው:: አስፈላጊ ከሆነ፣ የውይይቱ አካል ያልሆነ እንድ ሰው ተመድቦ ድንገተኛ የስልክ ጥሪዎች ካሉ እንዲቀበልና እንዲያስተላልፍ ማድረጉ ጠቃሚ ነው:: ይህ ሰው ጥሪዎችን ከተቀበለ በኋላ፣ በዕረፍት ሰዓት ሳይ መልእክት ሊያስተላልፍ ይችላል::

> 7ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሰዎች በጊዜ ወደ ስብሰባው ቦታ እለመምጣታቸው የሌሎችን ጊዜ ሲያባክንና ለውሳኔ መስጫ የሚያስፈልገውን ጊዜ ሲቀንስ የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) እንዳንድ ሰዎች ልክ በቀጠሮው ሰዓት የማይመጡት ለምን ይመስልሃል? ሐ) እንዳንድ ሰዎች ስብሰባውን አቋርጠው በመውጣት ወይም የስልክ ንግግር በማካሄድ የቡድኑን ጊዜ ሲያባክኑ የተመለከትከው እንዴት ነው? ይህ ሰዎች ለቦርድ ውሳኔና ለግል ጉዳያቸው ስለሚሰጡት ትኩረት ምን ያሳያል?

ለ. <u>ለስብሰባው የሚያስፈልጉትን ነገሮች የማዘጋጀት ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች የሚጠበቅባቸውን ተግባር በጊዜው በጥራት አይፈጽሙም</u>:: ዋና ጸሐፊው ወይም ሰብሳቢው ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊዎቹ ነገሮች በሙሉ መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ አለበት:: ይህም ማለት ስብሰባው የሚካሄድበትን ስፍራና ክፍል፣ እንዲሁም ለውሳኔ መስጫ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ሁሉ ማዘጋጀት አለባቸው ማለት ነው:: ተወካዮቹ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች እስኪዘጋጁ ድረስ መጠበቃቸው ወይም ለውሳኔው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች አለመዘጋጀታቸው ውድ ጊዜያቸውን

ያባክንባቸዋል:: መሪዎች ጥራት ያለው ውሳኔ ሊሰጡ የሚችሉት ትክክለኛ መረጃ ካላቸው ብቻ ነው::

ሐ. መሪዎች አዳዲስ አሳቦችን እያቀረቡ ውይይቱ ወደ ፊት እንዲሄድ በማድረግ ፋንታ የተነሡትን አሳቦች ይደጋግማሉ:: ምንም እንኳን አንድ ሰው የተናገረውን አሳብ መድገሙ በኢትዮጵያ ባህል መከባበርን የሚያሳይ ቢሆንም፣ ጊዜ ውድ በሆነባቸው ስብሰባዎች ላይ ይህንን ማድረጉ ሊበረታታ አይገባውም:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መናገር ያለባቸው አዲስና የተለየ አሳብ ካላቸው ብቻ ነው:: ቀደም ሲል በተነሣ አንድ አሳብ መስማማታቸውን ለመግለጽ ብለው ብዙ ከሚናገሩ፣ ምንም ዓይነት ተቃውሞ ሳያቀርቡ ዝም ብለው ቢቀመጡም ድጋፍ መስጠታቸው ይታወቃል::

መ. የቡድኑን ውይይት ወደ ፊት ፊቅ የማያደርግ ሪፖርት ማቅረብ:: የስብሰባ ጊዜዎችን ከሚያባክኑት ነገሮች አንዱ ለተነሣው ጉዳይ አልባት ለመስጠት የማያግዙ ረዣዥም ሪፖርቶችን ማቅረብ ነው:: እያንዳንዱ ተወካይ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት ያስባል:: ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሪፖርቶች ዝርዝር ጉዳዮችን የሚዳስሱ ናቸው:: በጽሑፍ ያልሰፈሩ በመሆናቸው ደግሞ፣ ሪፖርቶቹ እጥር-ምጥን ያለ አሳብ የያዙ አይሆንም:: ከአንዳንድ የቦርድ ስብሰባዎች መካከል ግማሽ ያህሉቹ የሚጠናቀቁት ሪፖርት በመስማት በመሆኑ፣ አምብዛም የቤተ ክርስቲያኒቱን ዋና ዋና ጉዳዮች አንሥቶ ለመወያየት ሳይቻል ይቀራል::

አስተዳዳሪ አካላት የስብሰባዎቹ ተካፋዮች የሚያቀርቧቸው ሪፖርቶች ዓላማ ምን እንደ ሆነ መረዳት አለባቸው:: በአመዛኙ ሪፖርቶች ሁለት ዓላማዎች አሏቸው:: በመጀመሪያ፣ ጠቃሚ መረጃዎችን ይሰጣሉ:: ሁለተኛ፣ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ለቦርዱ ተጠያቂዎች መሆናቸውን ያሳያሉ:: ስለሆነም በሽማግሌዎች ወይም ቦርድ ስብሰባዎች ላይ ሪፖርቶችን በምናቀርብበት ጊዜ እነዚህን ሁለት ዓላማዎች ለማሳካት መጣር አለብን::



ሪፖርቱን የሚያቀርቡት ሰዎች (ለምሳሌ፣ የሽማግሌዎች ቦርድ ከሆነ፣ ወንጌላውያን፣ መጋቢዎች፣ የሰንበት ት/ቤት አስተባባሪ፣ ወዘተ. . .፣ የአውራጃ ቦርድ ከሆነ ደግሞ፣ የአውራጃው ኃላፊና የእያንዳንዱ ንዑስ ቀጣና መሪ) ቦርዱ እግዚአብሔር በዚህ አገልግሎት አማካኝነት በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ምን እየሠራ እንዳለ የሚያስገነዝቡትን መረጃዎች ማስፈር አለባቸው:: ይህ በመረጃ ላይ ያተኮረ ሪፖርት ለቦርዱ አባላት የበለጠ ጠቃሚ እንዲሆን የሚከተሉት ነገሮች መሟላት አለባቸው::

ሀ. ሁለት ዓይነት የመረጃ ሪፖርቶች አሉ:: እነዚህም በጽሑፍና በቃል የሚቀርቡ ሪፖርቶች ናቸው:: ብዙውን ጊዜ በጽሑፍ የሰፈሩ ሪፖርቶች ሁለት ነገሮችን ያከናውናሉ:: 1) ሪፖርቱ በቀረበበት ጊዜ የተከናወኑትን ተግባራት፣ እና 2) ለታሪካዊ ሰነድነት ቤተ ክርስቲያን የምትፈልጋቸውን አሐዛዊ መረጃዎች ያካትታሉ:: የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ የሚያሳዩ ካልሆነ በቀር፣ አሐዛዊ መረጃዎች በቃል ለቦርዱ ባይቀርቡ ይመረጣል::

የቃል ሪፖርቶች የቤተ ክርስቲያንን ሠራተኞች ወይም የአውራጃ ቤተ ክርስቲያን ተግባራት በአጭሩ ማብራራት አለባቸው:: በዚህም ውስጥ የተሞከሩትንና የተከናወኑትን ተግባራት፣ ሊከናወኑ ያልቻሉትንና ይህም የሆነበትን ምክንያት በአጭሩ መግለጽ አስፈላጊ ይሆናል:: ለምሳሌ ያህል፣ አንድ የአውራጃ ቤተ ክርስቲያን ስላገኘው ከፍተኛ የምእመናን ዕድገት፣ መሪዎችን ለማሳደግ ስላከናወኗቸው ተግባራት፣ በጥሩ ሁኔታ ስለተከናወኑትና ስላልተከናወኑት ነገሮች ሪፖርት ማድረጋቸው ጠቃሚ ነው:: የዚህ ዓይነቱ መረጃ መሪዎች ከሌሎች ተሞክሮዎች በመማር ስሕተት ላለመፈጸም ማድረግ የሌለባቸውንና ለፍሬያማነት ማከናወን የሚገባቸውን ነገሮች እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል:: መረጃውን የሚሰጡ ሰዎች አላስፈላጊ ዝርዝር ጉዳዮችን ማብዛት የለባቸውም:: ለምሳሌ፣ ስንት የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ ቡድኖች እንዳሉ በጽሑፍ ሪፖርት ውስጥ ማስፈር ይቻላል:: ይህ ግን በቃል ሪፖርት ውስጥ መካተት የለበትም:: ሪፖርቱ መሪዎች የቤተ ክርስቲያን አካባቢውን ወይም አገልግሎቱን እንዴት

ሊያግዙ እንደሚችሉ የሚያሳያቸው ሊሆን ይገባል። ሁሉም ተወካዮች ሊያውቁት ይገባል ካልተባለ በቀር፣ አንድ ጉዳይ በቃል ሪፖርት ውስጥ መካተት የለበትም።

ለ. ከተቻለ ደግሞ፣ ሪፖርቶቹ በጽሑፍ ሰፍረው ከስብሰባው በፊት ለስብሰባው ተሳታፊዎች ሊዳረሱና እነርሱም አንብበው ሊመጡ ይገባል። በተለይ የቤተ ክርስቲያን መሪው ስለ አውራጃው አገልግሎቶች የጻፈው ሪፖርት በዚህ መንገድ ለተሰብሳቢዎች መዳረስ አለበት። አባላቱ ይህን ሪፖርት አንብበው በመምጣት በሪፖርቱ ውስጥ ስለ ተመለከቷቸው ነገሮች የቤተ ክርስቲያን መሪውን ሊጠይቁ ይችላሉ።

ሐ. ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት ሰው አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች በማጠቃለያነት በቃል መናገር እንጂ ማንበብ የለበትም። የቃል ሪፖርቶቹ የተሞከሩትን፣ የተከናወኑትንና እገዛ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በአጭሩ መግለጽ ይኖርባቸዋል። ሪፖርቱን የሚያቀርበው ሰው ሁሉንም ሰው በሚያሳስቡት ጉዳዮች ላይ ትኩረት መስጠት አለበት። በሪፖርቱ ውስጥ የሚቀርቡ አብዛኞቹ ዝርዝር ጉዳዮች ሁሉንም ሰው የሚመለከቱ አይሆኑም። ነገር ግን እግዚአብሔር ያደረገው አንድ ነገር ካለና ሌሎች ሰዎች ይህንኑ በመስማት የሚማሩ ከሆነ፣ መናገሩ ጠቃሚ ይሆናል።

መ. ከእያንዳንዱ ሪፖርት በኋላ፣ የቦርዱ አባላት አንዳንድ ነገሮች ስለ ተከናወኑባቸው መንገዶች ማብራሪያ የመጠየቅ ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል።

ሠ. ለቡድን ውይይት መቅረብ ያለባቸው አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ ጉዳዮች ብቻ መሆን አለባቸው። የተወሰኑ ሰዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ለሌላ ጊዜ ተትተው መሪውና የሚመለከታቸው ሰዎች መነጋገር አለባቸው።

2) የተወሰነ ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች ተጠያቂነታቸውን ለሽማግሌዎች ወይም ለቦርዱ የሚያሳዩት በሪፖርቶች አማካኝነት ነው። ስለሆነም፣ የመጋቢው ሪፖርት ሽማግሌዎች የሰጡትን ኃላፊነት እንዴት እየተወጣ እንዳለ የሚያሳይ መሆን አለበት።



የዋና ጸሐፊውም ሪፖርት ተግባራቱን እንዴት እየተወጣ እንዳለና ከሽማግሌዎች የተሰጡትን ሥራዎች እንዴት እያከናወነ እንዳለ የሚያሳይ መሆን አለበት። (ማስታወሻ፦ ብዙውን ጊዜ የዋና ጸሐፊው ሪፖርት ለአገልግሎታቸው ለዋና ጸሐፊው ወይም ለሽማግሌዎች ሰብሳቢ ተጠሪ የሆኑትን ወገኖች ሪፖርቶች ጠቅለል አድርጎ የሚያቀርብ መሆን አለበት። የታችኛው የአመራር አካል ባልደረባ ሪፖርት ማቅረብ ያለበት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ፣ የበታች አመራር ማናጀሮች በስብሰባው ላይ ተገኝተው በአገልግሎታቸው ላይ ለሚነሡት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት አለባቸው።) የቦርድ አባላት ሥራው ሙያው በሚጠይቀው ደረጃ አልተሠራም ወይም ቤተ ክርስቲያኒቱን ወደ ግቧ እየወሰዳት አይደለም የሚል አሳብ ካላቸው፣ አባላቱ የሪፖርቱን አቅራቢ ሊጠይቁትና ይበጃሉ የሚሏቸውን የመፍትሔ አሳቦች ሊሰነዝሩ ይገባል።

አንደኛው የተጠያቂነት ሪፖርት ዓይነት የፋይናንስ (የገንዘብ) ሪፖርት ነው። የዚህ ሪፖርት ዓላማ ገንዘቡ ምን ላይ እንደ ዋለ ማሳየት ብቻ ሳይሆን ገንዘቡ፣ አስተዋይነት በተሞላበት መንገድ ከጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ነው። ብዙውን ጊዜ መሪዎች አንዳንድ ነገሮችን ለማከናወን ዐቅደው በገንዘብ እጥረት ሳያከናውኑ መቅረታቸውን በሪፖርቱ ላይ ማመልከታቸው አስፈላጊ ነው።

ሽማግሌዎችና የቦርድ አባላት እነዚህን ሪፖርቶች ማዳመጥ ብቻ ሳይሆን፣ ጥያቄዎችንም መጠየቅ አለባቸው። እነዚህ ጥያቄዎች መሪዎቹ ግለሰቦቹ አከናውናለሁ ያሉትን አገልግሎትና የተሰጣቸውን ገንዘብ በትክክል ለመጠቀማቸው «ተጠያቂ» እያደረጓቸው መሆኑን የሚያሳዩ መሆን አለባቸው። መሪዎቹ በተጨማሪም ግለሰቦቹ ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ወይም ገንዘብ ካባከኑ፣ ባህሉ በሚፈቅደው መንገድ መገሠጽ አለባቸው። በተጨማሪም፣ መሪዎቹ አገልግሎቱ ስለሚሻሻልበት መንገድ ምክሮችን መስጠት አለባቸው። መሪዎቹ በሪፖርቱ ደስተኞች ካልሆኑ፣ ይህንኑ በግልጽ በማመልከት ግለሰቦቹ የሚያድጉበትን ዕድል መስጠት ይኖርባቸዋል። በቀረበው ሪፖርት እዝኖ ዝም ማለት

ለእግዚአብሔር ሥራ ግድየለሽ መሆን ነው - ነገሮችን ለመለወጥ ምንም አላደረግንምና። ግለሰቡም እርማት ሳይሰጠው ሊያድግ ስለማይችል፣ የሚያድግበትን መንገድ አላሳየነውም ማለት ነው። የሚሻሻልበትን መንገድ ካላሳየን ደግሞ፣ የእግዚአብሔርን ቅጣት እንዲጋፈጥ ትተነዋል ማለት ነው።

> 8ኛ ጥያቄ፦ የሽማግሌዎችን ወይም የቦርድ ስብሰባ ተካፍለህ የምታውቅ ከሆነ፣ ሪፖርቶችን በማቅረብ የሚባክነው ጊዜ ምን ያህል እንደ ሆነ ገምግም። ሀ) የጊዜው አጠቃቀም ጥሩ ነበር? መልስህን አብራራ። ለ) ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት ሪፖርቶቹ የተጫወቱት ሚና ምን ነበር? ሐ) የሪፖርት አሰጣጡ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን ምን ቢደረግ መልካም ነው ትላለህ?

16. ቦርዱ ውሳኔውን ከሰጠ በኋላ፣ የሚያስፈጽም ግለሰብ መመደብ አለበት። ይህ ግለሰብ የቤተ ክርስቲያን መሪ ወይም የቦርድ አባል ሊሆን ይችላል። ቦርዶች ከሚሠሯቸው ትልልቅ ስሕተቶች አንዱ የተሰጠውን ውሳኔ በኃላፊነት ተከታትሎ የሚያስፈጽም ሰው አለመመደብ ነው። ለአንድ ሰው ኃላፊነት ካልተሰጠ፣ ውሳኔው ተግባራዊ አይሆንም። ይህ ደግሞ ውሳኔውን ለመስጠት የዋለውን ጊዜ ከንቱ ያደርገዋል።

17. በቀጣዩ ስብሰባ ላይ ቦርዱ ውሳኔውን የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠው ግለሰብ ዐበይት ጉዳዮችን አስመልክቶ ሪፖርት እንዲያቀርብ መጠየቅ አለበት። ቦርዱ የተሰጠውን ውሳኔ እንዲያስፈጽም ኃላፊነት የተሰጠውን ሰው ተጠያቂ የሚያደርገው በዚህ መንገድ ነው።

> 9ኛ ጥያቄ፦ የቦርድ ወይም የኮሚቴ ስብሰባ ተካፍለህ ከሆነ፣ ከላይ ከተጠቀሱት 17 አሳቦች ቦርዱ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን የትኞቹ ከፍተኛ እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉ ይመስልሃል? እነዚህ አሳቦች ቡድኑ የሰጣቸውን ውሳኔዎች የበለጠ ጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉት እንዴት ነው?

እስካሁን ክህሎት ያለው መሪ ለመሆን የሚያስፈልጉትን ነገሮች በመመልከት ሳትደመም አልቀረህም። «ከዚህ ሁሉ ጣጣ ለምን እንደ ወትሯችን ዝም ብለን አንሠራም? ተፈጥሯችን ለዚህ የሚመች አይደለም። ለብስባዎች ላይ ተገኝተን ጠቃሚ ናቸው በምንላቸው ጉዳዮች ላይ ከመወያየት ያለፈ ልምድ የለንም!»



እያልክ ልታስብ ትችላለህ። በርግጥ፣ ነገሮች በዚህ መንገድ ተግባራዊ ሲሆኑ እንደሚችሉ ይታወቃል። ይሁንና፣ ለራስህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ብታቀርብ ሁኔታውን በበለጠ ለመረዳት ያስችልሃል። «ውሳኔዎችን ድሮ በለመዳችሁት ባህላዊ መንገድ በምትሰጡበት ጊዜ፣ ጥራት ያላቸውን ውሳኔዎች ለመስጠት ችላችኋል ወይስ ቤተ ክርስቲያን እንደ ቀድሞዋ መንቀሳቀሷን እንድትቀጥል ለማድረግ ብቻ ነው የቻላችሁት? አሁን የምትጠቀሙበት የውሳኔ አሰጣጥ ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ እየረዳት ነው ወይስ አይደለም? ፈጣንና በሚገባ የታሰበበትን ምላሽ የሚጠይቅ የተማረ አዲስ ትውልድ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየገባ በሚመጣበት ጊዜ፣ የድሮውን ዓይነት የውሳኔ አሰጣጥ ይዞ መዝለቅ ይቻላል?» ግንኙነቶችን በክህሎት ለመመሥረትና ጥሩ ውሳኔዎችን ለመስጠት በቂ ጊዜ ይወስዳል። ለኢየሱስና ለመንግሥቱ መስፋፋት በማሰብ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኞች ናችሁ? ለእግዚአብሔርና ለክብሩ ነገሮችን በክህሎት ለማከናወን መማሩ ተገቢ ነውን?

## ሁለተኛ ቀን

ሲሳወንድም በቅርቡ ከሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት በዲግሪ ተመርቋል። ይህ ትምህርት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን የማገልገል ዕድል ስለሚሰጠው፣ በጣም ደስ ብሎታል። በሥነ-መለኮት ኮሌጅ የተማራቸውን ብዙ ነገሮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሥራ ለመተርጎም ጓጉቷል። በአምልኮ፣ በአዳዲስ ነፍሳት የደቀ መዝሙርነት ትምህርትና ሽማግሌዎች ውሳኔ በሚሰጡባቸው መንገዶች ላይ ለውጥ ለማምጣት ተዘጋጅቷል። ነገር ግን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሲደርስ፣ ሽማሌዎቹ እንዴት እንደሚጠቀሙበት በግልጽ አላወቁም ነበር። ወጣትና ብዙ ልምድ ያላካበተ በመሆኑ፣ በብቃቱ ላይ ጥርጣሬ ነበራቸው። ብዙ ደመወዝም ሊከፍሉት አይችሉም ነበር። ሲሳወንድም አያሌ የለውጥ አሳቦችን ይዞ ሲቀርብ ተቃወሙት። «የእኛን መሳሳት ለመናገር እርሱ ደግሞ ማን ነው?» ይባባሉ ጀመር። በዚህም ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ የአገልግሎት ስፍራ ሊሰጡት አልፈለጉም። ብዙም ሳይቆይ፣

ሲላወንድም ይናደድ ጀመር፡፡ «እነዚህ ሽማግሌዎች ምንም ዓይነት ራእይ የላቸውም፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳላገለግልም እየተ ከላከሉኝ ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ ጥሩ ጥሩ ዕቅዶችና ራእዮች ይገፍ በቤተ ክርስቲያን ላይ ለውጥ እንዳላመጣ እያደረጉኝ ነው፣» ሲል አማረረ፡፡ ንዴቱ ወደ ቁጣ በመቀየሩ፣ የኋላ ኋላ ቤተ ክርስቲያኑን ትቶ በመሄድ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ተቀጠረ፡፡ ሲላወንድም እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንዲያመጣ የፈለጋቸውን ለውጦች ለማሳካት አልቻለም፡፡

**10ኛ ጥያቄ፡-** ሀ) እንደ ሲላወንድም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መደበኛ አገልግሎት ባለማግኘቱና ለውጥ ላመጣ አልችልም ብሎ በማሰቡ ተስፋ ስለ ቆረጠ ሰው ግለጽ፡፡ ለ) እንደ ሲላወንድም ዓይነቱ ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ምን እንዲያደርግ ትመክረዋለህ?

## ክህሎት ስድስት፡- በቤተ ክርስቲያን እንዴት ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ማወቅ

እንደ ሲላወንድም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለውጥ ለማምጣት የሚፈልጉና ነገር ግን ሰዎች ለመለወጥ አለመፈለጋቸውን በመረዳት የሚቸገሩ ሰዎች አሉ፡፡ አብዛኛው ሰው በለመደው መንገድ መቀጠሉ ያስደስተዋል፡፡ በመሆኑም፣ ለውጥን አሜን ብሎ አይቀበልም፡፡ እድገት አስቸጋሪ ሂደት ነው፡፡ ነገር ግን እድገት ክሌለ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይና ዕቅዶች በመጠቀም እርሱ የሚፈልገውን ዓይነት ሕይወት ልንመራ እንችልም፡፡ አንድ መሪ ምእመናን ክርስቶስን በመምሰል ሕይወት እንዲያድጉ የማበረታታት ኃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ለውጥ ለማምጣት እንደሚችሉ ማወቃቸው አስፈላጊ ነው፡፡

ይሁንና፣ መሪዎች ካልተጠነቀቁ፣ በዓለማዊ የአመራር መንገድ ለውጥ ለማምጣት ሊሞክሩ ይችላሉ፡፡ ኃይላችንንና ሥልጣናችንን ተጠቅመን ሰዎች የምንፈልጋቸውን ነገሮች እንዲያደርጉ እናዝዛቸዋለን፡፡ ነገር ግን፣ ይህንን በምናደርግበት ጊዜ አያሌ ችግሮች ይከሰታሉ፡፡ በመ<u>ጀመሪያ</u> <u>ደረጃ</u>፣ እግዚአብሔር «አገልጋይ መሪዎች» እንድንሆን እንጂ በሰዎች ላይ አምባገነን በመሆን ተለወጡ ብለን እንድናዝዛቸው አልጠራንም፡፡ <u>ሁለተኛ</u>፣ ኃይልንና እዝን መጠቀም ለውጥ የሚያመጣ ቢመስልም፣ ጫና ጋብ ሲልላቸው፣ ሕዝቡ ወደ ቀደመው አኗኗራቸው ይመለሳሉ፡፡ የሰዎች አስተሳሰብ እስካልተቀየረ ድረስ፣ ዘለቄታዊ ለውጥ ሲመጣ አይችልም፡፡ ይህንን የመንግሥት ባለሥልጣናት ሕዝቡ ዛፍ እንዳይቆርጥ በማስጠንቀቅ ቆርጠው በተገኙት ላይ ቅጣት ከሚጥሉበት ሁኔታ መመልከት ይቻላል፡፡ ለጊዜው ይህ ችግሩን ቢያንስ በከፊል ለመቅረፍ ችሎ ነበር፡፡ (ሰዎች ለመለወጥ በማይፈልጉበት ጊዜ እንጨት በድብቅ እንደ መሸጥ ያለውን ያለመለወጥ ብልሃት ይጠቀማሉ፡፡) ወዲያውኑ መንግሥት ቁጥጥሩን ላላ በሚያደርግበት ጊዜ፣ ሕዝቡ ዛፍ ወደ መቁረጡ ይመለሳል፡፡ ሕዝቡ የዛፍ ጥቅም ስላልገባው፣ ምትክ ሳይተክል ዛፍ እንዳይቆርጥ የሚነገረውን መልእክት ተግባራዊ በማድረግ ለውጥ ለማምጣት አልፈለገም፡፡ <u>ዘለቄታዊ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው ሰዎች የአንድን አዲስ ነገር እሴት ተመልክተው በፈቃደኝነት ክተለወጡ ብቻ ነው</u>፡፡ እስተዋይ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለውጥ እንዴት እንደሚመጣ በመረዳት አስተሳሰባቸውን የሚቀይሩበትን ብልሃት ይፈጥራል፡፡ ጳውሎስ እንዳስተማረን፣ የዓለምን እስተሳሰብና እተገባበር መከተል የለብንም፡፡ ነገር ግን *በአእምሯችን መታደስ* ተግባራችንን መለወጥ አለብን፡፡ (ሮሜ 12:2 እንብብ፡፡) መሪዎች እንደ መሆናችን፣ ምእመናን ክርስቶስን በመምሰልና ክርስቶስን የሚያስከብሩ ነገሮችን በማከናወን እንዲያድጉ አስተሳሰባቸውንና እተገባበራቸውን እንድንለውጥ እግዚአብሔር ኃላፊነት ሰጥቶናል፡፡

መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ክህሎት ለማዳበር ሲያስታውሷቸው የሚገባቸው ነጥቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

**ለውጥ የማምጣት ብቃት የሚጀምረው አንድ መሪ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመለወጥና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እድገት ለማምጣት እንደሚችል ሲያምን ነው፡፡**

አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ ተናገረው፣ የሕይወትና የአገልግሎት ውጤታማነት ለሚያጋጥመን ሁኔታ ያለን «አመለካከት» ውጤት ነው። ይህ በተለይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እርሱ ወደሚፈልገው አቅጣጫ በመምራቱ በኩል እውነት ነው። አመለካከታችን (ወይም ባሕርያችን) ለምእመናኑ መለወጥ ወይም አለመለወጥ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። ለውጥ በጸሎትና በመንፈስ ቅዱስ የማስቻል ሥራ የሚካሄድ መሆኑ እሙን ነው። ይህም ሆኖ፣ የመሪዎች አመለካከት፣ በእግዚአብሔር ላይ ለመደገፍ መፍቀዳቸውና እግዚአብሔር ለውጥ ያመጣል ብለው መስማራታቸው እድገትን ለማምጣት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል። ስለሆነም፣ መሪዎች እግዚአብሔር ለለውጥ እንዲጠቀምባቸው ከፈለጉ፣ ለሕይወትና ለሁኔታዎች አዎንታዊ አመለካከት መያዝ አለብን።

ሰዎች ለሁኔታዎች በሚሰጡት ምላሽ ለሁለት ይከፈላሉ።

1. አብዛኞቹ ሰዎች ተግባራቸውንና የለውጥ ችሎታቸውን ሁኔታዎች እንዲወስኑ ይፈቅዳሉ። አብዛኞቹ ሰዎች ሌሎች ሰዎችና ሁኔታዎች እንዲቆጣጠሯቸው ይፈቅዳሉ። እነዚህ ለሁኔታዎች ምላሽ ወደ መስጠቱ አቅጣጫ ስለሚያዘነብሉ፣ «እንደ ሁኔታው የሚቀያየሩ» ተብለው ይጠራሉ። እነዚህ ሰዎች ጊዜው ጥሩ ሲሆንላቸው፣ የተጨማሪ ትምህርት ወይም የተሻለ ሥራ ዕድል ሲያገኙ ይደሰታሉ። ነገር ግን ነገሮች በማይስኩላቸው ጊዜ፣ ምንም ዓይነት ጥረት ሳያደርጉ ቁጭ ብለው ሌሎችን ለደረሰባቸው ችግር ይወቅሳሉ። የሚለወጡትም ሌሎችን ስላዩ እንጂ በሚገባ ስላሰቡበትና ስለ ፈለጉት አይሆንም። በአመዛኙ አንድ ሰው እንደ ሁኔታው የሚቀያየር መሆኑን አስቸጋሪ ሁኔታዎችን አስመልክቶ ከሚናገረው ቃል ተነሥቶ መረዳት ይቻላል።

ሀ. ለሁኔታው ሌሎች ሰዎችን *ይወቅሳሉ*። «ወላጆቼ ገበሬ ዎች ባይሆኑ ኖሮ። ይህ የሆነው ያ ጎሳ የእኛን ጎሳ ስለሚጠላ ነው። የመጋቢነትን ስፍራ ስላልሰጡኝ፣ ሳገለግል አልችልም» በማለት ለገጠማቸው ችግር ሌሎች ሰዎችን ይወቀሳሉ።



ለ. እነዚህ ሰዎች አስቸጋሪውን ሁኔታ ለመለወጥ እኔ <u>ምንም ሳደርግ አልችልም</u> ወደ ማለቱ ያዘነብላሉ። በሁኔታው ታስ ረው ጥንቃቄ በተሞላበት ዕቅድና ተግተው በመሥራት ሁኔታውን ሊለውጡ እንደሚችሉ ለማሰብ ይቸገራሉ። «እነዚህ መሪዎች እንደ ሆነ አይሰሙንም። አንድ ነገር እንዲያደርጉልን መጠየቁ ምን ዋጋ አለው?» ሲሉ ያማርራሉ ወጣቶቹ። «በባህላችን መሠረት የምንሠራው በዚህ መንገድ ነው። ልንለውጥ አንችልም።»

ሐ. እንዲህ ዓይነት ሰዎች ሌሎችን *በቅናት ቢመለከቱም* የሚቀኑባቸው ሰዎች ከደረሱበት ለመድረስ ምንም ዓይነት ጥረት አያደርጉም። «እገሌና እገሌ የቤተ ክርስቲያን መሪ ልጆች ናቸው። ለዚህ ነው ኪቦርድ የሚጫወቱት። እኔም ኪቦርድ ብጫወት ደስ ይለኝ ነበር። ነገር ግን እኔ የአገልጋይ ልጅ ስላልሆንኩ፣ እንድጫወት አይፈቅዱልኝም። ተስፋ የሌለው ነገር ነው፣» ይላሉ።

መ. ከሁኔታዎች ጋር የሚቀያየሩ ሰዎች <u>በስሜታቸው ይመራሉ</u>። «የዚያን ጎሳ ሰዎች አልወዳቸውም። ሁሌም የሚጥሩት እኛን ከአመራር ለማራቅ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነገሮችን በምንፈልገው መንገድ እንድናከናውን ስለ ማይፈልጉ ተናድጃለሁ።» ተስፋ በመቁረጥ ሌሎች ሰዎችን ያማሉ።

ሠ. እነዚህ «የቢሆን ኖሮ» ዓለም ሰዎች ናቸው። ይህንንም ስንል <u>ሊሆን ይችላል ያሉትን በመናፈቅ</u> እንዲህ እያሉ ሲያዝኑ ይደመጣሉ ማለታችን ነው። «ይህ ቢሆን ኖሮ፣ ቤተ ክርስቲያናችን ታድግና ትለወጥ ነበር። የገጠር ቤተ ክርስቲያን ባንሆን ኖሮ፣ ለወንጌል ስርጭት ብዙ ገንዘብ ይኖረን ነበር። ከሌላ ቦታ የመጣ ወንጌላዊ ቢኖረን ኖሮ፣ ቤተ ክርስቲያናችን ታድግ ነበር። ገንዘብ ቢኖረን ኖሮ፣ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ እንገነባ ነበር ወይም ወንጌላውያንን ወደ ሌላ ቦታ እንልክ ነበር።» እነዚህ ሰዎች በችግር ላይ ስለሚያተኩሩ፣ እምብዛም የለውጥ ጥረት አያደርጉም።

| |
|---|
| 11ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ሲላወንድም «ከሁኔታዎች ጋር የሚለዋወጥ» ሰው የሆነው በምን መንገድ ነው? ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መደበኛ አገልግሎት ባይሰጠውም፣ እንዴት ለውጥ ለማምጣት ጥረት ሊያርግ ይችል እንደ ነበረ ግለጽ። |

2. ሲላወንድም ለውጥ ማምጣት የሚቻልባቸውን መንገዶች እንደ መፈለግ፣ ሽማግሌዎቹ አሳቡን ወዲያውኑ ባለመቀበላቸውና ደመወዝ የሚከፈልበት አገልግሎት ባለማግኘቱ፣ አገልግሎቱን ትቶ መሄዱ «ከሁኔታዎች ጋር የሚለዋወጥ» ሰው ያሰኘዋል:: ቀስ በቀስ ሁኔታውን ለመቀየርና አሳቡን ተግባራዊ ለማድረግ ከመጣር ይልቅ፣ ሽማግሌዎቹን ነበር ተወቃሽ ያደረገው::

ለውጥ የሚያመጡ መሪዎች ሁኔታዎች እንዲቆጣጠሯቸው በመፍቀድ ፈንታ ራሳቸው ሁኔታዎችን የሚቆጣጠሩ ናቸው:: ምሁራን እነዚህን ልዩ ግለሰቦች «ለሁኔታዎች የማይበገሩ» በማለት ይጠሯቸዋል:: እነዚህ ሰዎች የሆነ ነገር እንዲፈጸም ወይም እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት የሆነ ሰው አንድ ነገር እንዲያደርግ በመጠበቅ ፈንታ ራሳቸው እርምጃ የሚወስዱ ናቸው:: እነዚህ ሰ ዎች እንደ ማንኛውም ሰው የሚፈልጉትን በቀላሉ ለማሳካት የሚያዳግቱ ፈተናዎችና ችግሮች ይገጥሟቸዋል:: መሪዎች አሳባቸውን ሊቃወሙ ይችላሉ:: የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ተ ለውጠው የእግዚአብሔርን ራእይና ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ መለወጥ ያስፈልጋቸው ይሆናል:: ቤተ ክርስቲያናቸው ድሀ ወይም ብዙ የተማረ ሰው የሌለባት የገጠር ቤተ ክርስቲያን ልትሆን ትችላለች:: ነገር ግን ሰዎች ዕቅዱን ስለ ተቃወሙ ወይም ለመለወጥ ስላልፈለጉ ተስፋ ከመቁረጥና ሌሎች ሰዎችንና ሁኔታ ዎችን ከመውቀስ ይልቅ፣ ለውጥ ማምጣት የሚቻልባቸውን መንገዶች ይቀይሳሉ:: ለሁኔታዎች የማይበገሩ መሪዎች ለውጥ ለማምጣት የቆረጡ ሲሆኑ፣ ይህም በባሕርያቸውና በንግግራቸው ውስጥ የሚንጸባረቅ ነው::

ሀ. ለሁኔታዎች የማይበገሩ ሰዎች ሌሎችን ለመውቀስ አይፈልጉም:: ወላጆቻቸውን ወይም ያልተማሩና ድሆች መሆናቸውን እንሥቶ ማማረሩ እርባና እንደሌለው ያውቃሉ:: ሌ ሎችን መውቀሳችንን እስከ ቀጠልን ድረስ፣ በሁኔታዎች ቁጥጥር ሥር የምንኖር ተስፋ የሌለን ሰዎች ነን:: ወቀሳውን በሌላው ሰው ላይ አላክከን ቁጭ ካልን ምንጊዜም ለውጥ ሊመጣ አይችልም::



ሁሉም ለውጥ የሚጀምረው ለውጥ ለማምጣት ኃላፊነትን በመውሰድ ነው::

ለ. ለሁኔታዎች የማይበገሩ ሰዎች የሁኔታዎች እስረኞች መሆናቸውን ለመቀበል አይፈልጉም:: ሁልጊዜም ሁኔታውን ለመቀየር አንድ የሚያከናውኑት ነገር እንዳለ ያምናሉ:: «እርግጥ ነው ወላጆቼ ድሆች በመሆናቸው ምክንያት ወደ ትምህርት ቤት ሊልኩኝ አልቻሉም:: ነገር ግን የጫማ መጥረጊያ ዕቃዎችን እንዲገዙልኝ ብጠይቃቸውስ? ቀን ጫማ እየጠረግኩ ማታ ብማርስ?» እያሉ በማሰብ ለውጥ የሚያመጡባቸውን ቀዳዳዎች ይፈልጋሉ::

ሐ. ለሁኔታዎች የማይበገሩ ሰዎች ሌሎች ካገኙት ልዩ ዕ ድል የተነሣ የተቀዳጁትን ስኬት በቅናት እየተመለከቱ ጊዜያቸውን አያባክኑም:: ነገር ግን ነገሮችን ለመለወጥ ሊያደርጉ በሚችሉት ነገር ላይ ትኩረት ያደርጋሉ:: «በርግጥ፣ ሽማግሌዎች ልጆቻቸው ኪቦርድ እንዲጫወቱላቸው ድጋፍ ይሰጧቸዋል:: ነገር ግን ብዙ ጊዜ ወስጄ በመለማመድ ከፍተኛ ችሎታ ካገኘሁ፣ ሌሎች እንድጫወት መጠየቃቸው አይቀርም:: በሰርግ ወይም በልዩ ፕሮግራሞች ላይ ኪቦርድ ልጫወት እችላለሁ:: በዚህ ዓይነት ከሁሉም የላቀ ችሎታ እንዳለኝ ሲያውቁ፣ በመዘምራን ውስጥ እንዳገለግል ይጋብዙኛል፣» የሚል ምክንያት ያቀርባሉ::

መ. ለሁኔታዎች የማይበገሩ ሰዎች የሚኖሩት በፈቃዳቸው እንጂ በስሜታቸው አይደለም:: ከእነርሱ የተሻለ ጥቅም ያገኙትን ሰዎች በመጥላት ምንም እንደማያገኙ ያውቃሉ:: እንዲህ ዓይነት ሰ ዎች የሚደርሱባቸውን ኢ-ፍትሐዊነቶች ወደ ጎን በመተው በመርሕ ላይ የተመሠረተ ሕይወት ለመምራት ይመርጣሉ:: ኢ-ፍትሐዊነትንና ጎሰኝነትን ላለማስፋፋት በማሰብ በፍትሐዊነትና በትክክለኛነት ለመመላለስ ይወስናሉ:: ሁኔታው ለእነርሱ በሚመች ሁኔታ የሚቀየርበትን መንገድም ለመፈለግ ይጥራሉ:: «ሽማግሌ ዎች የአገልግሎት ስፍራ ባይሰጡኝም፣ በፈቃደኝነት አዳዲስ አማኞችን ብረዳና ራሴን ዝቅ አድርጌ በሚፈልጉት መንገድ ሽማግሌዎችን ብረዳቸው፣ ወዘተ. . . አንድ ቀን እግዚአብሔር

እንደ ጠራኝ በመረዳት ስፍራ ይሰጡኛል። በዚህ ጊዜም ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ ሽማግሌዎችን ለመሰወጥ እችላለሁ፤» ብለው ያስባሉ።

ሠ. ለሁኔታዎች የማይበገሩ ሰዎች «እንዲህ ቢሆን ኖሮ» እያሉ በማሰብ ጊዜያቸውን ለማባከን አይፈልጉም። ነገር ግን ሁልጊዜም ለመቆጣጠር የሚችሏቸውንና ለውጥ የሚያመጡባቸውን ነገሮች ይፈልጋሉ። «ሽማግሌዎች መጋቢ ሊያደርጉኝ አልፈለጉም። ነገር ግን በሰፈሬ ብዙ የተጎዱና የእግዚእብሔርን ቃል ማወቅ ያለባቸው ሰዎች አሉ። እነርሱን ልረዳቸው እችላለሁ። በሰፈራችን ውስጥ ላሉት ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል ላስተምር እችላለሁ። ሽማግሌዎች እነዚህን አገልግሎቶች ስላልከለከሉኝ፣ በዚህ መንገድ ማገልገል እችላለሁ፤» ብለው ያስባሉ። የሚገርመው፣ በዚህ ዓይነት አገልግሎት ሲጀምሩ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ እያደገ ይመጣል። አንድ ቀን እግዚአብሔር የሕዝቡን፣ በተለይም የሽማግሌዎቹን፣ ዓይን ይከፍትና ግለሰቡ በመጋቢነት ወይም በወጣት አገልጋይነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲሠራ ይመድባሉ።

12ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሲላወንድም ለሁኔታዎች የማይበገር ቢሆንና ያጋጠመውን ሁኔታ ለመለወጥ ቢሞክሮ ኖሮ፣ አሁንም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገልና ለውጥ ለማምጣት ሊያደርግ የሚገባቸው ነገሮች ምን ምን እንደ ሆኑ ዘርዝር። ለ) ሲላወንድም ለሁኔታዎች ባይገዛና ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉትን ተግባራዊ ዘዴዎች ቢጠቀም፣ ምን ዓይነት ውጤቶችን ሊያመጣ እንደሚችል ግለጽ።

አንዲት የሥነ-መለኮት ትምህርት ምሩቅ «እግዚአብሔር የአገልግሎት በር እንዲከፍትልኝ ጸልዩልኝ» አለች። እውነት የአገልግሎት በር ተዘግቶባት ነበር? አልተዘጋባትም። እርሷ የተመለከተችው ለሁኔታዎች ከመገዛት አንጻር ነው። የፈለገችው መሪዎች መደበኛ የአገልግሎት ስፍራ እንዲሰጧት ነበር። «የሴቶች ወይም የወጣቶች መሪ ቢያደርጉኝ ኖሮ . . . » የሚል አቋም ይዛ ነበር። ከዚህም የተነሣ፣ እግዚአብሔር የሰጣትን የጸጋ ስጦታና ሥልጣና ሳትጠቀም ዝም ብላ ተቀመጠች። ማንም ሰው



የአገልግሎት በር ሊዘጋብን አይችልም። መደበኛ የአገልግሎት ዕድል ሊነፍጉን ይችላሉ። ነገር ግን በሺዎች የሚቆጠሩ መደበኛ ያልሆኑ የአገልግሎት ዕድሎች ከፊታችን አሉ። የትኛውም አገልጋይ ወደ ሰዎች ቤት በመሄድ ከእነርሱ ጋር አብረን እንዳንጸልይና እንዳናበረታታቸው ሊያደርገን አይችልም። ወይም ከሰዎች ጋር በመገናኘት እንዳንመሰክርላቸው ወይም በእምነታቸው ያድጉ ዘንድ እንዳንረዳቸው ሊከለክሰን አይችልም። ይህ እውነት ሆኖ ሳለ፣ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ምሩቃን አገልግሎት አጣን ብለው ያማርራሉ። ከሁኔታዎች ጋር የመቀያየር ባሕርያቸው በዙሪያቸው ያሉትን የአገልግሎት ዕድሎች ተጠቅመው በሰዎች ሕይወት ውስጥ ለውጥ እንዳያመጡ ዓይኖቻቸውን ይጋርድባቸዋል። እነዚህ ምሩቃን በታማኝነት እግዚአብሔርንና ሰዎችን ቢያገለግሉ፣ እግዚአብሔር እነዚህ ሰዎች ሌሎችን በማገልገልና እንዲለወጡ ተጽዕኖ በማድረስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል። እግዚአብሔርን በታማኝነትና በትሕትና በማገልገል ሰዎች በእምነታቸው እንዲያድጉ የምንረዳቸው ከሆነ፣ እግዚአብሔር በጊዜው ወደ መደበኛው አገልግሎት ደረጃ ያደርሰናል። ይህ የሚሆነው ግን ለሕይወታችንና ላጋጠመን ሁኔታ ኃላፊነትን በመውሰድ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ስንጥር ብቻ ነው።

**ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአገልግሎታቸው ለውጥ የማምጣት ሂደትን የጀመሩት ሊቆጣጠሩ የሚችሏቸውን ነገሮች በማከናወን እንጂ፣ ሊቆጣጠሩ የማይችሏቸውን ነገሮች ለማድረግ በመሞከር አይደለም።**

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በችግሮች የታጠረ ነው። ምን ጊዜም ለማከናወን የምንፈልጋቸውን ነገሮች ለማካሄድ የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል ማግኘት አይቻልም። ዕቅዶቻችንንና ሕልሞቻችንን እውን ለማድረግ የሚያስችል በቂ ገንዘብ አይኖርም። ከሁኔታዎች ጋር እንደሚለዋወጡ ሰዎች ማሰብ ብንጀምር፣ «ምንም ማድረግ አንችልም፤» ብለን እጃችንን አጣጥፈን እንቀመጣለን። ልናደርግ የምንችለው ነገር ቢኖር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነገሮች በተቻለ

መጠን በሰላማዊ ሁኔታ እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ነው ብለን ልንደመድም እንችላለን:: በሰዎችም ላይ ልናማርር እንችላለን:: ይህም እነዚህ ችግሮች እንዲከሰቱ በፈቀደው አምላክ ላይ በተዘዋዋሪ ማማርን ያሳያል::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዕቅዶቻቸውንና ራእያቸውን እውን ማድረግ በሚጀምሩበት ጊዜ፣ ወዲያውኑ እነዚህ ችግሮች ይከቧቸዋል:: ለረዥም ጊዜ የቆመን መኪና ማስነሣቱ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን መኪናው አንድ ጊዜ ከተነሣ፣ ጉዞውን እንዲቀጥል ማድረጉ አስቸጋሪ አይሆንም:: መሪዎች ለውጥ ለማምጣት እግዚአብሔር እንዲጠቀምባቸው ከፈለጉ፣ የሚችሏቸውን ነገሮች ፈልገው ከዚያ ሊጀምሩ ይገባል:: በዚህ ጊዜ ችግሮችን የማሸነፍና ለውጥ የማምጣት ችሎታችን ይጎለብታል::

የዕድገት ሂደት እንዳይቋረጥ እነዚህን ችግሮች እንዴት ልናሸንፍ እንችላለን? በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ሊያጋጥሙን የሚችሉ ሦስት ዓይነት ችግሮች እንዳሉ መረዳት አለብን:-

1. <u>በቀጥታ የምንቆጣጠራቸው ነገሮች</u>:: አንዳንድ ጊዜ ሁኔታውን ለመለወጥ ቀጥተኛ የሆነ እርምጃ ልንወስድ እንችላለን:: ሊላወንድም ሊቆጣጠር የሚችላቸው አያሌ ነገሮች ነበሩ:: መራርነት እንዳይሰማው በመሪዎች ላይ የነበረውን ስሜት ሊቆጣጠር ይችል ነበር:: «ምንም ሳደርግ አልችልም፣» የሚለውን አስተሳሰብ ሊቆጣጠር ይችል ነበር:: በዙሪያው የነበሩትን አያሌ አነስተኛ የአገልግሎት ዕድሎችም ሊቆጣጠር ይችል ነበር:: ይበልጥ እግዚአብሔርን በሚያስደስት መንገድ እንዲኖሩ ሊያስተምር የሚችላቸው ሰዎች ነበሩ:: ሊላወንድም መጀመሪያ አንድ ወጣት፣ ከዚያም ሁለት፣ ከዚያም ሦስት ቢያስተምርና ቢለውጥ ኖሮ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ የቤተ ክርስቲያኒቱን ምእመናን የማሳደግ ራእዩን እውን ሊያደርግ ይችል ነበር::

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪ እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይ ለመጀመር በምንፈልግበት ጊዜ፣ ልንጀምር የምንችላቸው አያሌ ነገሮች አሉ:: ሳጋጠሙን ችግሮችና ፈተናዎች



የሚኖረንን አመለካከት ልንቆጣጠር እንችላለን:: ችግሮቹ የማይቻሉ ናቸው ብሎ ከማሰብ ይልቅ፣ እግዚአብሔር አመለካከታችንን በመለወጥና እነዚህ ችግሮች እርሱ እንድናሸንፍ የሚያስችለን መሆናቸውን እንድንረዳ እንዲያግዘን ልንጠይቅ እንችላለን:: ብቃት ያላቸውን ዕቅዶች ልናወጣ እንችላለን:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሆንን፣ ለምእመናን የለውጥን አስፈላጊነት የሚያስተምሩትን ሰዎች ልንፈልግ እንችላለን:: ምእመናን ለማከናወን የምንፈልጋቸውን ነገሮች እንዲረዱ የሚያስችሉትን ሠንጠረዦች ልናዘጋጅ እንችላለን:: ሁልጊዜም መሪዎች የለውጥን ሂደትና እግዚአብሔር የሰጣቸውን ዕቅዶችና ራእይ የማከናወኑን ተግባር ለመጀመር ሊያከናውኑ የሚችሏቸው አያሌ ነገሮች አሉ::

> 13ኛ ጥያቄ:- በትምህርት 10 ለቤተ ክርስቲያናችሁ ያዘጋጀሃቸውን ዕቅዶች ተመልከት:: እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪ በቀጥታ የምትቆጣጠራቸውን ነገሮች በመዘርዘር እንዴት የለውጥን ሂደት ልትጀምር እንደምትችል ግለጽ::

2. እንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ <u>በተዘዋዋሪ መንገድ የሚቆጣጠራቸው</u> ወይም ተጽዕኖ የሚያሳድርባቸው ነገሮች አሉ:: ማናችንም ብንሆን የሌላውን ሰው ባሕርይ ልንቆጣጠር እንችልም:: አንድ ሰው እንደ ተናገረው፣ «የአንድ ሰው ልብ የለውጥ እጀታ ያለው በውስጡ ብቻ ነው:: በሩ ሊከፈት የሚችለው ከውጭ ባለው ሰው ሳይሆን፣ ከውስጥ ባለው ሰው አማካኝነት ብቻ ነው::» ሁሉም ለውጥ የሚመጣው ግለሰቡ ለመለወጥ ፈቃደኛ ሊሆን እንጂ፣ እኛ መሪዎች እንዲሆን የምንፈልገውን ነገር እንዲሆን ስናዝዘው አይደለም::

እንግዲህ ማንንም በጉልበት ለመለወጥ እስካልቻልን ድረስ፣ ምን ልናደርግ እንችላለን? ልንቆጣጠር የምንችላቸውን ነገሮች በማከናወን ምእመናን ለለውጥ በሮቻቸውን እንዲከፍቱ ልናበረታታቸው እንችላለን:: ለምሳሌ፣ አለመተማመን አመራራችንን እየገደበው ከሆነና ሰዎች ገንዘብ እንዳይሰጡ እየተከላከለ ከሆነ፣ በምእመንና በአመራሩ መካከል መተማመን የሚሰፍንባቸውን መንገዶች ልንቀይስ እንችላለን:: ለምእመናን የግል እንክብካቤና

ትኩረት በመስጠት እግዚአብሔር የሰጠንን መልእክት በምናካፍላቸው ጊዜ፣ በፈቃደኝነት እንዲቀበሉን ልናበረታታቸው እንችላለን:: ወይም ደግሞ የመግባባት ብቃታችንን ልናሳድግ እንችላለን:: ሰዎች ምን ለማድረግ እየሞከርን እንዳለንና ይህንንም ለምን እንደምናደርግ እንዲገነዘቡ ልናደርግ እንችላለን:: እውነቱን ካወቁ በኋላ፣ አዲስ ነገር ለመጀመር ፈቃደኞች ሊሆኑ ይችላሉ:: ወይም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተደማጭነት ያላቸውን ቡድኖች እንፈልጋለን:: ወጣቶች የሚሰሙት ማንን ነው? ብዙውን ጊዜ አንድ የሚሰሙት ወጣት ይኖራል:: ስለዚህ ከዚህ ወጣት ጋር በመጸለይ ዕቅዳችንን እናካፍለዋለን:: ተደማጭነት ወዳለው ሽማግሌ ወይም የሴቶች መሪ እንሄዳለን:: እንዲህ ዓይነት ሰዎችን ምክር ስንጠይቃቸውና ስለ ራእዩ አብረናቸው ስንጸልይ፣ እኛ በማንችለው መንገድ ራእዩን ወደ ሕዝቡ የማስተላለፍ ብቃት ይኖራቸዋል::

| |
|---|
| 14ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሲላወንድም የኋላ ኋላ የፈለገውን የአገልግሎት ደረጃ ለማግኘት እንዲችል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የገጠመውን ችግር እንዴት በተዘዋዋሪ መንገድ ሊለውጥ ይችል ነበር? ለ) ምእመናን ለመለወጥ ፈቃደኞች እንዲሆኑ መሪዎች በተዘዋዋሪ ሊያደርጉ የሚችሏቸው አንዳንድ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? |

3. <u>ለመቆጣጠር የማንችላቸው</u> ሁኔታዎች አሉ:: የተወለድንበትን ቦታ የመምረጥ ዕድል አልነበረንም:: በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ከብዙ የዓለም አገሮች ባነሰ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ይገኛሉ:: ይህ ደግሞ የገንዘብን ውስንነት አስከትሏል:: በመሆኑም፣ ለአገልግሎት መኪና የሌለንና ለአገልግሎት የምንፈልጋቸውን ሰዎች ሁሉ ለመቅጠር የሚያስችል ገንዘብ የሌለን የመሆኑን ሁኔታ ልንቆጣጠር እንደማንችል እንገነዘባለን:: ቀደም ሲል የተፈጸሙትንና የማንወዳቸውን ነገሮች ለመቆጣጠር እንደማንችልም እናውቃለን:: ቀደም ሲል በተፈጸሙት ስሕተቶች ሳቢያ የሚጠራጠሩንን ሌሎች ጎሳዎችም ልንቆጣጠር አንችልም:: እነዚህን የማንቆጣጠራቸውን ነገሮች በማሰብ ወይም እንዲህ ባይሆን ኖሮ እያልን በመመኘት የምናጠፋው ጊዜ አይኖረንም::



ጊዜያችንንና ጉልበታችንን በእነዚህ ልንቀየር በማንችላቸው ነገሮች ላይ ከማዋል ይልቅ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ልንለውጥ በምንችላቸው ነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን:: አንድን ሁኔታ የምንለውጠው በቀጥታ ለመቆጣጠር ከምንችላቸው ነገሮች በመጀመር ነው:: ከዚያ በኋላ የተወሰኑ ነገሮችን በማድረግ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽዕኖ ልንሳድር ስለምንችልባቸው ነገሮች እናስባለን:: በተዘዋዋሪ መንገዶች በሌሎች ላይ ተጽዕኖ በምናሳድርበት ጊዜ፣ በቀጥታ የምንቆጣጠራቸው ነገሮች ይበዙልናል::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን፣ እግዚአብሔር በሰጠንና በቀጥታ ተጽዕኖ ለማሳደር በምንችልባቸው የራእዩና የዕቅዱ ክፍሎች እንጀምራለን:: እግዚአብሔር እንዲረዳን በመጠየቅ ጾምና ጸሎት እናደርጋለን:: ከሌሎች ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ስብሰባዎችን እናዘጋጃለን:: ወይም ደግሞ እንዴት ነገሮችን ልንለውጥ እንደምንችል ለማቀድ ኮሚቴዎችን እናዋቅራለን:: ተለውጥ እንዲመጣ በምንፈልጋቸው ነገሮች ላይ አንድ ሰው ተከታታይ ትምህርት እንዲሰጥ እንጠይቃለን:: ሌላም ሌላም ነገር እናደርጋለን::

ከዚያ በኋላ የዕቅዱን ተፈጻሚነት በሚገድቡ ነገሮች ላይ ያለንን ተጽዕኖ ለማሳደግ የሚያስችሉንን መንገዶች እንፈልጋለን:: ሕዝቡ ከራእዩ ጋር እንዳይተባበር የሚያግድ አለመተማመን አለ? እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ፣ መተማመን እንዲፈጠር ተጨማሪ ተግባራትን እናከናውናለን:: ለውጥ እንዳይመጣ የሚከላከሉ አንዳንድ ተደማጭነት ያላቸው ሽማግሌዎች አሉ? በዚህ ጊዜ እነዚህ ሰዎች አዳዲስ አሳቦችን ለማስተናገድ ልባቸውን እንዲከፍቱ ለማገዝ ከእነርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት ለማሻሻል ጥረት እናደርጋለን:: ሰዎች ለእግዚአብሔር ሥራ በልግስና ለመስጠት ይቸገራሉ? የቤተ ክርስቲያን ምእመናን መሪዎች ገንዘባችንን በአግባቡ ከጥቅም ላይ አያውሉም የሚል ጥርጣሬ ካላቸው፣ ገንዘቡ በሙሉ የት እንደሚውል የሚረዱበትን የግልጽነት መርሕ እንቀይሳለን:: እንዲሁም ደግሞ የእግዚአብሔርን

ዕቅድና ራእይ እውን ለማድረግ ምእመናን በልግስና መስጠታቸው አስፈላጊ መሆኑን በግልጽ የሚያስረዱ ታላላቅ ስባኪዎችን ልንጠቀም እንችላለን:: በተዘዋዋሪ መንገድ በምንቆጣጠራቸው ነገሮች ላይ መሥራት ካልጀመርን፣ ለውጥ ልናመጣም ሆነ ለውጥ የሚመጣበትን መንገድ ልናመቻች አንችልም:: ችግሮችና ፈተናዎች ለውጡን ይቋቋማሉ:: ግባችን ሰዎች በፈቃዳቸው እግዚአብሔርን እንዲሰሙና እንዲለወጡ፣ ከዚህም የተነሣ በሕይወታቸውና በተግባራቸው ይበልጥ ክርስቶስን እየመሰሉ እንዲሄዱ ማገዝ ነው::

ይህንን እውነት ወንድሞቹ ለባርነት በሸጡት ዮሴፍ ሕይወት ውስጥ እንመለከታለን:: ለባርነት ለምን ተዳረግኩ ብሎ ሕይወቱን ለምሬት አሳልፎ ቢሰጥ ኖሮ፣ ዕድሜ ልኩን ባሪያ ሆኖ ይቀር ነበር:: በባርነቱ ወይም ወንድሞቹ ለባርነቱ እርሱን በሸጡበት ሂደት ላይ ምንም ዓይነት ቁጥጥር የማካሄድ አቅም አልነበረውም:: ነገር ግን ባሕርዩን በቀጥታ መቆጣጠር ይችል ነበር:: ስለሆነም፣ እግዚአብሔር የባርነት ሕይወቱን እንዲቆጣጠር ለእርሱ ራሱን አሳልፎ ለመስጠት መረጠ:: እንዲሁም ዮሴፍ ጊዜውን መቆጣጠር ይችል ነበር:: ስለዚህም ትርፍ ጊዜውን ሁሉ በመጠቀም ጥረት ያለው ሥራ መሥራት ቻለ:: በየቀኑ መልካም ባሕርይ በማሳየት፣ ተግቶ በመሥራት፣ ታማኝ በመሆንና ከሌሎች ባሪያ ዎች ሁሉ በበለጠ ጥሩ ሥራ በመሥራት በጲጥፋራ ላይ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ማሳደር ይችል ነበር:: እግዚአብሔርም የዮሴፍን ባሕርይና ትጋት በመጠቀም የጲጥፋራ ቤትና በኋላም በእስር ቤትና በግብጽ አገር ሁሉ ላይ አለቃ ሊያደርገው ቻለ:: ዮሴፍ ተስፋ ቆርጦ ራሱን ለምሬት አሳልፎ ቢሰጥ፣ ይህ ሁሉም አይሳካም ነበር:: እግዚአብሔር ዮሴፍን ከፍ ለማድረግ ባሕርያቱንና ድርጊቶቹን፣ በነገሮች ላይ የነበረውን ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ቁጥጥር ተጠቅሟል:: እግዚአብሔር እኛንም ወደ ታላቅ የተጽዕኖና የአመራር ደረጃ ለማሳደግ የምንችላቸውን ነገሮች በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ የመቆጣጠር ምርጫዎቻችንን ለመጠቀም ይፈልጋል::



ይህንን አመለካከት የሚያሳይ አንድ አስተዋይ መሪዎች ሊጠቀሙበት የሚገባ ጸሎት አለ:: ጸሎቱም፣ «ጌታ ሆይ፣ መለወጥ የምችላቸውንና መለወጥ ያለብኝን ነገሮች የምለውጥበትን ብርታት፣ የማይለወጡትን ነገሮች የምቀበልበትን ጸጋ፣ እንዲሁም በሁለቱም መካከል ያለውን ልዩነት የማውቅበትን ጥበብ ስጠኝ::»

> 15ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊቆጣጠሯቸው እንደማይችሉ በመዘንጋት ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን የሚያፈስሱባቸውን ነገሮች ዘርዝር:: በእነዚህ ነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ ጊዜ ማባከን የሚሆንበትን ምክንያት አብራራ:: ለ) ሕይወትህንና እግዚአብሔር የሰጠህን የግል ራእይ አጢን:: 1) ራእዩን ለመፈጸም እንድትችል የሚያግዙህንና በቀጥታ ልትቆጣጠር የምትችላቸውን ነገሮች ዘርዝር:: 2) ራእዩን ለመፈጸም እንድትችል የሚያግዙህንና በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽዕኖ ልታሳድር የምትችልባውን ነገሮች ዘርዝር::

**አስተዋይ መሪዎች የቤተ ክርስቲያን ምእመናን እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ ለመሆንና ለማድረግ የሚሻ አመለካከት እንዲላበሱ ለማድረግ ይጥራሉ::**

ሁልጊዜም እድገት ለውጥን ያስከትላል:: ምእመናን በእድገት አስፈላጊነት ላይ ከተማመኑ በኋላ፣ እግዚአብሔር እንድንሆን የሚፈልገውን ሁሉ ለመሆንና እንድናደርግ የሚፈልገውን ማድረጉ ቀላል ይሆናል:: ብዙውን ጊዜ ሰዎች በአንድ አቅጣጫ በሚያድጉበት ጊዜ፣ በሌሎችም አካባቢዎች ለመለወጥ ዝግጁዎች ይሆናሉ:: ጎጂ ገጽታ ያላቸው አያሌ ለውጦች አሉ:: እድገታችን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚዎች ለመሆን ወደሚፈልገው አቅጣጫ የሚወስደን መሆን አለበት:: አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የተለያዩ ለውጦችና እድገቶች መኖራቸውን ማወቅ አለበት:: ይህም በለውጦች ላይ ከሚገባው በላይ ትኩረት በማድረግ እግዚአብሔር በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ ለማየት የሚፈልገውን እውነተኛ ለውጥ ቸል እንዳይል ያግዘዋል::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው ሊያመጡ የሚችሏቸው አራት ዓይነት ለውጦች::

በአመዛኙ፣ አዳዲስ ነገሮች ሲከናወኑ በምናይበት ጊዜ፣ ለውጥ እየተካሄደ ነው ብለን እናስባለን። ወይም ደግሞ አስፈላጊ (እንደ አስተሳሰብና የባሕርይ ለውጥ) እና ዘለቄታዊ የሆኑትን ነገሮች ልብ ሳንል፣ ለመለወጥ በሚቀልሉ (እንደ አለባበስ ባሉ) ነገሮች ላይ ትኩረት እናደርጋለን። አራት ዓይነት ለውጦች አሉ።

***ሀ. የውጫዊ ነገሮች ለውጥ።*** ይህ እንደ አለባበስ ወይም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር ያሉትን ነገሮች የሚመለከት ነው። ይህ በቀላሉ የሚካሄድ ለውጥ ነው። ቤተ ክርስቲያን በቀላሉ መዋቅራዊ ለውጥ ልታደርግ ትችላለች። (ለምሳሌ፣ ቤተ ክርስቲያን በቀላሉ አንድ የአውራጃ ቀጣና ልትጨምር ትችላለች።) እንዲህ ዓይነቱ ለውጥ ብዙ መስጠትን ስለማይጠይቅ፣ በቀላሉ ሊካሄድ የሚችል ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም እንዲህ ዓይነት ለውጦችን በመመልከት፣ እያደጉና እየተለወጡ መሆናቸውን ይናገራሉ። ቀደም ሲል የሣር ክዳን ሕንጻ የነበራቸው ሲሆን፣ አሁን ግን የቆርቆሮ ቤት ሠርተዋል። ቀደም ሲል መዘምራኖቻቸው በክራር ይዘምሩ የነበረ ሲሆን፣ አሁን ግን ኪቦርድ ገዝተዋል። የመዘምራንም ልብስ ገዝተዋል። እነዚህ ውጫዊ ለውጦች በቀላሉ የሚካሄዱ ከመሆናቸውም በላይ፣ የሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ብዙም ሳይለወጥ ሊደረጉ የሚችሉ ናቸው። የሚያሳዝነው፣ ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲህ ዓይነት ነገሮችን በመመልከት እነዚህ መንፈሳዊ እድገት መኖሩን የሚያሳዩ ናቸው ብለው ማሰባቸው ነው። መሪዎች በእንደዚህ ዓይነት ለውጦች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚፈልገው ዓይነት መንፈሳዊ ብስለት ምን ጊዜም ሊመጣ አይችልም። የሚያሳዝነው፣ አብዛኛው የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ የሚፈስሰው ወደ ብስለት የሚደረገውን ግስጋሴ ሊያግዙ ለማይችሉ ለእንዲህ ዓይነት ነገሮች ነው።

**ለ. ለዎች የሚጠቀሙት የቴክሎጂ ዓይነት ለውጥ።** የምንኖረው ፈጣን ቴክኖሎጂያዊ ለውጦች በሚካሄዱበት ዓለም ውስጥ ነው። ምንም እንኳን እነዚህን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ለመጠቀም ተጨማሪ ሥልጠናዎችን መውሰድ አስፈላጊ ቢሆንም፣ በዚህ በኩል



የሚደረጉ ለውጦች ቀላልና ሥቃይ የማያስከትሉ ናቸው። ለምሳሌ፣ አንድ ፈረስ ሲጋልብ የኖረ ሰው በቀላሉ መኪና መንዳትን ሊማር ይችላል። በወረቀትና እስክሪብቶ ሲጠቀም የኖረ ሰው በቀላሉ ኮምፒዩተር ሊማር ይችላል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የዚህ ዓይነቱ ለውጥ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እያደገች ነው ብለው እንዲያስቡ እየተፈታተናቸው ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲህ ዓይነት ለውጦችን በመፈለጋቸው፣ ለምእመኖቻቸው «ኮምፒዩተር መግዛት አለብን» ወይም «ለሥራችን መኪና ያስፈልገናል» ይላሉ። እግዚአብሔር የሚሰጠንን አዳዲስ ነገሮች ለመጠቀም መማሩ አስፈላጊ ነው። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ነገሮች «መሣሪያዎች» ብቻ መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል። በመሆኑም፣ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ለማየት የምንፈልጋቸውን ለውጦች ሊያመጡልን አይችሉም። አስደሳች ነገሮች ቢመስሉም፣ አንድ ትምህርት ቤት በተሻለ መንገድ መጋቢዎችን እንዲያሠለጥን ሊያደርጉት አይችሉም፤ ቤተ ክርስቲያንም መንፈሳዊ ብስለትን እንድትላበስ አያስችሏትም። ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ያሠለጠነው ትምህርት ቤትንም ሆነ ኮምፒዩተር ሳያይ ነው።

**ሐ. የድርጊት ለውጥ።** አሁን አስፈላጊ ወደ ሆነው የለውጥ ደረጃ እየገባን ነው። እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለዎች በባሕርያቸውና በአስተሳሰባቸው እንዲለወጡ እንፈልጋለን። በመሆኑም፣ ሰዎች ጠጪዎች እንዳይሆኑ፣ ሚስቶቻቸውን እንዳይደበድቡ፣ ወሲባዊ ኃጢአቶችን እንዳይፈጽሙ እናስተምራለን። በጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ፣ አሥራታቸውን እንዲሰጡ፣ ወዘተ. . . እናስተምራለን። እነዚህ ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓይነት ለውጦች የተሻሉ መሆናቸው ግልጽ ነው። ብዙዎቹ ስብከቶቻችን ሰዎች የተቀደሰ ሕይወት እንዲመሩ የሚጠይቁ በመሆናቸው በዚህ የለውጥ ደረጃ የሚቀርቡ ናቸው። ምእመኖቻችን እግዚአብሔርን የሚያስከብሩ ሰዎች መሆን ካለባቸው ባሕርያቸው መቀየር አለበት። ባሕርይን መቀየር እንደ አለባበስ ወይም ቴክኖሎጂያዊ አጠቃቀም ቀላል እንዳልሆነ ከልምድ የምናውቀው ነው። ለምሳሌ፣ ትምህርት ቢሰጣቸውም ሰዎች

በሰዓቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን አይመጡም:: እግዚአብሔር የሰጠንን ራእይና ዕቅድ ለመፈጸም በምንጥርበት ጊዜ፣ የሰዎችን አስተሳሰብ ለመለወጥ እንፈልጋለን:: ላልዳኑ ጎረቤቶቻቸው እንዲመሰክሩ፣ አስራት እንዲሰጡ፣ በማኅበረሰባቸው ውስጥ ድሆችን እንዲረዱ እንፈልጋለን:: በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትኩረት መስጠት ካለባቸው የለውጥ ዓይነቶች አንዱ የምእመናን የባሕርይ ለውጥ ነው::

መ. የአስተሳሰብ ለውጥ ወይም ጥልቅ የሕይወትና የእሴቶች ግንዛቤ:: (ማስታወሻ:- ሰዎች የአምነት ለውጥ ሳያደርጉ ባሕርያቸውን ሊለውጡ ይችላሉ:: ለምሳሌ፣ ባሎች ሚስቶቻቸውን ላይመቱ ይችላሉ:: ነገር ግን አሁንም ሚስቶቻቸው ከእነርሱ የበታች እንደ ሆኑ ሊያስቡ ይችላሉ:: ነገር ግን ሰዎች የአስተሳሰብ ለውጥ በሚኖራቸው ጊዜ፣ ተግባራቸውም ይለወጣል::) ክርስቶስ ስለ ደቀ መዝሙርነት በሚያስተምርበት ጊዜ፣ ወሲብን አለመፈጸም ወይም ሰውን አለመግደል የመጨረሻው ቅድስና ተደርጎ ሊታይ እንደማይገባ አስረድቷል:: ነገር ግን የልብን ዝንባሌ የሚያሳዩ የአይታና የቁጣ ቃላት ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑን አመልክቷል (ማቴ. 5:21-30):: ክርስቶስ ከምእመናን የሚፈልገው እውነተኛውና ዘላቂው ለውጥ የልብና የጥልቅ እምነት ለውጥ ነው:: እነዚህ ውስጣዊ ነገሮች ካልተለወጡ፣ እግዚአብሔር ከሰዎች የሚፈልገው ቅድስናና ጽድቅ እውን ሊሆኑ አይችሉም::

ይሁን እንጂ፣ ይህ እጅግ ከባዱ ለውጥ ነው:: ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሎች ባህሎች ካሏቸው ወገኖች ጋር በሰላም እንዲቀመጡ ልናደርግ እንችላለን:: ነገር ግን ከተለያዩ ጎሳዎች የመጡ ሰዎች ልባዊ ፍቅር እንዲለዋወጡና ለራሳቸው ጎሳዎች ምንም ዓይነት አድልዎ እንዳያሳዩ ልናደርግ አንችልም:: ባሎችና ሚስቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብረው እንዲቀመጡ ወይም መንገድ አብረው እንዲሄዱ ማድረግ ይቻላል:: ነገር ግን ባል ሚስቱን በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ እኩል እንደ ሆነችና የእግዚአብሔር መንግሥት እኩል ወራሽ እንደ ሆነች አድርጎ እንዲያስብ ማድረጉ ከባድ ነው (1ኛ ጴጥ. 3:7):: የቤተ ክርስቲያን



መሪዎች የራስ ወዳድነት ፍላጎቶችን እንዳያስተናግዱ፣ ለቤተሰቦቻቸው ወይም ለቤተ ክርስቲያናቸው እንዳያዳሉ ማድረጉ በአመራር ደረጃ ከሌሎች ጋር አብረው ውሳኔ እንዲሰጡ ከማድረግ የበለጠ ከባድ ነገር ነው:: በአመራሩ እግዚአብሔርን ለማስከበርና ምእመናን እግዚአብሔር የሚፈልገባቸውን እንዲሆኑ የሚሻ መሪ ሁልጊዜም በእነዚህ ውስጣዊ ለውጦች ላይ ትኩረት ያደርጋል:: በማኅበረ ምእመናኑ ውስጥ ጥልቅ የእምነት ለውጥ እስካላየ ድረስ፣ ለእግዚአብሔር ወሳኝ በሆኑት ጉዳዮች ገና አለመለወጣቸውን ያውቃል::

| |
|---|
| 16ኛ ጥያቄ:- ሀ) ባለፈው ዓመት ውስጥ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የተመለከትካቸውን ሁለት ውጫዊ ለውጦች ጥቀስ:: እነዚህ ለውጦች ዘለቄታ ያለው መንፈሳዊ እድገትና ብስለት አምጥተዋል? ለ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ የተመለከትካቸውን ሁለት ቴክኖሎጂያዊ ለውጦች ግለጽ:: እነዚህ ለውጦች ጥልቅ መንፈሳዊ ለውጥ ማምጣት አለማምጣታቸውን ግለጽ:: ሐ) በምእመናን ባሕርይ ላይ የተመለከትካቸውን ሁለት ለውጦች ጥቀስ:: እነዚህ ነገሮች የመንፈሳዊ ብስለት እድገት ምልክቶች መሆን አለመሆናቸውን ግለጽ:: መ) ባለፉት ሁለት ዓመታት በምእመናን እምነትና እሴቶች ላይ ያየሃቸውን ሁለት ለውጦች ጥቀስ:: ይህ የመንፈሳዊ ብስለት እድገት ምልክት መሆን አለመሆኑን ግለጽ:: |

ለውጥ የማይቀር እስከ ሆነ ድረስ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው መንገድና ለጥሩ ምክንያቶች እንዲለወጡ ማበረታታት ይኖርባቸዋል::

ዛሬ በዓለማችን ውስጥ ለውጦች በፍጥነት በመካሄድ ላይ ናቸው:: በአንድ የትውልድ ዘመን ብቻ ባህላዊ እሴቶች ያሏቸው ገበሬዎች ተቀይረው የምዕራባውያንን ባሕርይ ለማሳየት ሲሞክሩ ይታያል:: ወጣቶች እንደ ወላጆቻቸው የድሮ ባህል ተከታዮች ሳይሆኑ፣ ዘመናውያን ለመሆን ይፈልጋሉ:: የሰዎች አለባበስ እየተቀየረ ነው:: ቀደም ሲል ሴቶች አጭር ቀሚስ መልበሳቸው ተቀባይነት አልነበረውም:: አሁን ግን በትላልቅ ከተሞች ውስጥ ብዙ ወጣት ሴቶች አጫጭር ቀሚሶችን ይለብሳሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን ለውጦች ሊያስቆሙ አይችሉም:: ነገር ግን ጥሩ

ትምህርት በመስጠት ለውጦቹ እግዚአብሔርን ወደሚያስከብር አቅጣጫ እንዲሄዱ ማደረግ ይችላሉ።

ለውጦች የሚመጡት ከሁለት ዓይነት ጫናዎች ነው። አንደኛ፣ «ውጫዊ» ጫናዎች። አንድ ሰው ወይም ቤተ ክርስቲያን ከውጫዊው ዓለም በሚደረግባቸው ጫናዎች ሊለወጡ ይችላሉ። በመሆኑም፣ ዘመናዊ ወጣት መሆን ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በቴሌቪዥን ላይ የሚሰጥ ትምህርት ወጣቱ በቴሌቪዥን ላይ የሚያያቸውን ሰዎች የሚመስል አለባበስ እንዲከተል ሊገፋፋው ይችላል። ወይም ደግሞ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎቶች (ለምሳሌ፣ የፈውስ አገልግሎት፣ ሚሲዮናውያንን ከኢትዮጵያ ውጭ መላክ) ቤተ ክርስቲያን ተመሳሳይ ነገሮችን እንድታደርግ ጫና ሊያሳድሩባት ይችላሉ። አንዲት ቤተ ክርስቲያን ትልቅ የመዘምራን ቡድን በማዘጋጀት ስኬታማ ሆናለች ተብሎ ከታሰበ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትልቅ የመዘምራን ቡድን እንዲያዘጋጁ ጫና ይደረግባቸዋል። ውጫዊ ጫናዎችና የሚያመጧቸው ለውጦች ጠቃሚም ጎጂም ሊሆኑ ይችላሉ።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን የሚጋፈጧቸውን ውጫዊ ውጥረቶች መረዳት አለባቸው። ምእመኖቻችን ያለ ምንም መመሪያ ወዲያ ወዲህ እንዲዋልሉ ከፈቀድን፣ ወይም ጥሩዎቹን ለውጦች እንዲመርጡና መጥፎዎቹን እንዲቃወሙ ካላበረታታን፣ ውጫዊዎቹ ለውጦች ሰዎች ዓለምን እንዲመስሉ ሊያደርጉ ይችላሉ። ሮሜ 12:2 በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ውስጥ እንደ ተመለከተው፣ «ዓለም ራሱን እንድትመስል እንዲያደርግህ አትፍቀድለት፣» ይላል። ይህም ተፈጥሯዊና ቀላል ለውጦች ከዓለም የሚመጡ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው።

<u>ሁለተኛ</u>፣ «ውስጣዊ» ጫናዎችም ለውጦችን ያመጣሉ። ውስጣዊ ጫናዎች እንደ ግለሰብ ወይም እንደ ቤተ ክርስቲያን የምንመርጣቸው ነገሮች ናቸው። እነዚህም በእምነታችንና በተግባራችን እንድንለወጥ የሚያደርጉን ናቸው። እግዚአብሔር ለአንድ ቤተ ክርስቲያን በሚሰጣቸው ራእዮችና ዕቅዶች፣ በእግዚአብሔር ቃል ትምህርት፣ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ወቀሳና ማስቻል



አማካኝነት አማኞች ሁሉ ወደ መንፈሳዊ ብስለትና እግዚአብሔርን ወደሚያስከብሩ ተግባራት የሚመራ ውስጣዊ ጫና ሊሰማቸው ይገባል።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ትኩረት ማድረግ ያለባቸው በዚህ ጉዳይ ላይ ነው። በውጫዊ መዋቅራዊ ወይም ቴክኖሎጂያዊ ለውጦች ላይ ትኩረት ከማድረግ፣ ወይም የሌሎችን አብያተ ክርስቲያናትና የዓለምን መንገዶች (ለምሳሌ፣ የሌቶች አመራር ጉዳይ) ከመከተል ይልቅ፣ እንዴት መለወጥ እንዳለብን ለመረዳት ቃሉን እንድናጠና እግዚአብሔር ፈቃዱ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ በምናጠናበት ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንዴት እንድናምንና እንድንመላለስ እንደሚፈልግ ያሳየናል። ወይም ደግሞ እንደ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎታችንንና ሕይወታችንን በመገምገም ወደ ፊት ለእኛ የእግዚአብሔር ራእይ ምን እንደ ሆነ እንረዳለን። አሁን ባለን ሁኔታና እግዚአብሔር እንድንሆን በሚፈልገው ነገር መካከል ያለው ልዩነት ውስጣዊ ውጥረት እንዲሰማን ያደርጋል። መንፈስ ቅዱስም ይህንን በመጠቀም ለማደግና ለመለወጥ ያለንን ፍላጎት ይጨምራል።

| |
|---|
| 17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ክርስቲያኖችና አብያተ ክርስቲያናት በአካባቢያቸው ባሉት ውጫዊ ጫናዎች ምክንያት የሚለወጡባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህና በቤተ ክርስቲያናችሁ ለውጦችን ለማምጣት ውስጣዊ ጫናዎችን የተጠቀመባቸውን መንገዶች ዘርዝር። |

ምእመናን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያመጣቸውን ለውጦች የሚቀበሉበትን አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማድ ረግ አለባቸው፡-

ሀ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ደካማና ጠንካራ ጎኖች ለማወቅና ለውጥ የሚያስፈልጋቸውን አካባቢዎች ለመለየት ይችሉ ዘንድ፣ የምእመናንን አጠቃላይ ሁኔታ መገምገም አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን ቀደም ሲል ምን ያህል ታላቅ እንደ ነበ ረች ማውራቱ ጥቅም የለውም። እግዚአብሔርን የሚያሳስበው ሰ ዎች አሁን መንፈሳዊ ብስለት ማግኘታቸው ነው። የቤተ ክርስቲያን

መሪዎች እንደ ሎዶቅያ በመንፈሳዊነታቸው እንዳይኩራሩ መጠንቀቅ አለባቸው (ራእይ 3:17):: በዕድገታችን ልንቀጠል የምንችለው በየትኞቹ መንገዶች መለወጥ እንዳለብን ስንገነዘብ ነው:: ጠንካራ ጎኖቻችንን ማወቁ ለእግዚአብሔር ክብር እነዚህን ጥንካሬዎች እንዴት ማሳደግ እንዳለብን እንድናውቅ ያስችለናል:: ደካማ ጎኖቻችንን ማወቃችን ደግሞ በተሻለ ሁኔታ እግዚአብሔርን ለማስከበር እንችል ዘንድ ድክመቶቻችንን ለማስወገድ የሚያስችሉንን ዕቅዶች እንድንነድፍ ያስችለናል::

ለ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያሉትን አገልግሎቶች ይዘው ለመቀጠል ወይም ውጫዊ ነገሮችን (ለምሳሌ፣ የተሻለ ሕንጻ፣ የተሻለ የድምጽ ማጉያ፣ ወዘተ. . .) ለማዘጋጀት ከመሞከር ይልቅ፣ በሰዎችና በመንፈሳዊ ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው:: እግዚአብሔር በዋናነት የሚፈልገው የሰዎችን መንፈሳዊ ሕይወት መገንባትን ነው:: ዋንኛ ፍላጎቱ ማራኪ አገልግሎቶችን፣ ሕንጻዎችን፣ መዘምራንን፣ ወይም የሙዚቃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት አይደለም:: በእግዚአብሔር ዓይኖች፣ አንዲት ቤተ ክርስቲያን የምትገመገመው እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን አገልግሎቶች በማሟላቷ ወይም ባለማሟላቷ (በትምህርት 9 ውስጥ የሚገኘውን ሠንጠረዥ ተመልከት) እና ሰዎች በኤፌሶን 4:13-16 ውስጥ በተጠቀሰው መንገድ መንፈሳዊ ብስለት በማግኘታቸውና ባለማግኘታቸው ነው::

ሐ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎቶች በተለመደው መንገድ እንዲቀጥሉ ከመፈለግ ይልቅ፣ ለችግሮች መፍትሔ በመፈለግና መንፈሳዊ እድገት እንዲመጣ በማበረታታት ላይ ትኩረት ሊያደርጉ ይገባል:: እንደ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ችግሮች በመፍታቱና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በርጋታ እንዲንቀሳቀሱ በማድረጉ ተግባር ላይ እናተኩራለን:: ለወንጌላውያን ስለሚከፈል ደመወዝ፣ በምእመናን መካከል የተነሡትን ውዝግቦች ማርገብ ስለሚቻልባቸው መንገዶች፣ ለመዘምራን ልብስ መግዣ የሚሆን ገንዘብ ስለምናገኝባቸው መንገዶች፣ ወዘተ. . . እንወያያለን:: ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ነገሮች የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ባሉበት ሁኔታ እንዲቀጥሉ ከማድረግ ውጭ፣ በለውጥና በእድገት ላይ እንድናተኩሩ አያስችሉንም:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች (እና ምእመናን) የዕድገትን ድባብ ለመፍጠር እንዲችሉ በችግሮቻቸውና ለምን እግዚአብሔር በሚፈለገው መንገድ እንደማያድጉ ትኩረት ለጥተው መወያየት ይኖርባቸዋል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር በሰጣቸው ራእዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ለምን ያንን ራእይ ለመፈጸም እንዳልቻሉ መጠየቅ አለባቸው:: ምእመናንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር እጅግ አስፈላጊ ነው በሚለው መንገድ የሚለወጡት በእነዚህ ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት በሚረዱበት ጊዜ ነው::

መ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በእድገት ሂደቱ ውስጥ ምእመናንን ማሳተፍ ይኖርባቸዋል:: ምእመናን እንዲያድጉ ማስገደድ አይቻልም:: ነገር ግን ምእመናን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በመፈለጋቸው ለማደግ እንዲሹ የሚያደርግ ሁኔታ መፍጠር አለብን:: እድገት የሚመጣበትን ሁኔታ የምናመቻቸው በሚከተሉት መንገዶች ነው:: 1) እግዚአብሔር ለሕይወታችን የሚፈልገውን ነገር በጥንቃቄ በማስተማር፣ 2) በታዛዥነት እየተመላለስን ወይም በመንፈሳዊ ሕይወታችን እየበሰልን አለመሆናችንን በማሳየት፣ 3) ምእመናን ድክመት በሚያሳዩባቸው ሁኔታዎች ላይ እንዴት እድገትን ሊያመጡ እንደሚችሉ በማሳየት:: መንፈስ ቅዱስ ይህንን በመጠቀም ምእመናን ለማደግ እንዲፈልጉ ሊያነሣሣቸውና ሕይወታቸውን እንዲለውጡ ሊያስችላቸው ይችላል::

ሠ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናንን በእድገት ጎዳና ላይ መምራት ይኖርባቸዋል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ፈጣንና ከፍተኛ ለውጥ ለማምጣት አይፈልጉም:: ለዚህም ምክንያቱ መእመናን እንዲህ ዓይነቱን እድገት ሊቃወሙ ስለሚችሉ ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን እግዚአብሔር ወዳሰበላቸው ራእይ ለመድረስ የሚያስችሉትን እርምጃዎች በትንሽ በትንሹ ማካሄድ ይኖርባቸዋል:: ባለማቋረጥ የቤተ ክርስቲያንን ፕሮግራሞች በመገምገም (በየስድስት ወሩ ወይም ይህንን

በሚመስል የጊዜ ርቀት) እነዚህ ፕሮግራሞች እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ራእይ የሚደረገውን ጉዞ እያገዙት መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርብናል:: ነገሮች የተለየ መልክ እንዲይዙ በመፈለጋችን ብቻ ለመለወጥ መጣር የለብንም:: ይልቁንም፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሰጠውን ራእይ በመፈጸሙ ላይ ማተኮር አለብን:: የምንፈልገው የመንፈሳዊ ብስለት እድገት ለማምጣት ነው:: እማኞች በበለጠ ከመመስከራቸው ውስጥ ምን ዓይነት ለውጦችን እንመለከታለን? ከምእመናን የእግዚአብሔር እውቀት ምን ዓይነት ለውጦችን እናያለን? በእማኞች መካከልና በማኅበረሰቡ ውስጥ ባሉ የማያምኑ ሰዎች መካከል የታየው የፍቅር እድገት ምን ዓይነት ነው? በግምገማችን አማካኝነት ለመንፈሳዊ እድገትና ለራእዩ ተፈጻሚነት ውጤታማ የሆኑትንና ያልሆኑትን ነገሮች እንለያለን:: በዚህ ጊዜ እድገትን ማምጣት እንድንችል የማያግዙንን ነገሮች በፍጥነት ልንለውጥ እንችላለን:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አንድ ነገር ቀደም ሲል ውጤታማ ስለሆነ አሁንም ውጤታማ መሆኑ አይቀርም በሚል ግምት ዝም ብለው መቀጠል የለባቸውም:: ከዚህ ይልቅ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያንዳንዱን አገልግሎት መገምገምና ሰዎች ክርስቶስን እንዲመስሉ ማገዝ አለማገዙን ማረጋገጡ ተገቢ ነው::

*18ኛ ጥያቄ:- መንፈሳዊ እድገት የሚመጣበትንና የቤተ ክርስቲያን ራእይ የሚፈጸምበትን ሁኔታ ለመፍጠር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሁን ከሚያደርጉት የተለየ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ግለጽ::*

## በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለውጥ በማምጣቱ በኩል የመሪዎች ሚና::

ቀደም ሲል እንደተመለከተው፣ የተግባርና የእምነት ለውጥ ሊመጣ የሚችለው በግለሰቡ ፍላጎት ነው:: ማንም የቤተ ክርስቲያን መሪ ምእመናንን በግድ ሊለውጥ እንደማይችል ማስታወስ አለብን:: ነገር ግን አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደ እማኝ ለኢየሱስ ባለው ፍቅርና እርሱን ለማስደሰት በመፈለጉ ምክንያት ለለውጥ



እንዲነሣሣ ሊያግዘው ይችላል:: «አንድን ፈረስ ወደ ውኃ ትወስደዋለህ እንጂ፣ ውኃ ልታጠጣው አትችልም» የሚል አባባል አለ:: ይሁንና፣ ውኃው ውስጥ ፈረሱ የሚወደውን ጨው በመጨመር እንዲጠጣ ማድረግ ይቻላል:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ምንም እንኳን ሰዎች በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉና ለእግዚአብሔር ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ሊቸግረን ቢችልም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰዎች እግዚአብሔርንና ራእዩን ለመፈጸም እንዲፈልጉ ልናነሣሣቸው እንችላለን::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለውጥን ለማምጣት ስላላቸው ሚና የሚከተሉት ነጥቦች ዐበይት እውነቶችን ያስረዳሉ:-

1. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለእድገትና ለውጥ እንቅፋት እንዳንሆን መጠንቀቅ አለብን:: ብዙውን ጊዜ ከምእመናን በላይ ለውጥንና እድገትን የሚቃወሙት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው:: ይህ በተለይ የቤተ ክርስቲያን መሪዎቹ በግል ሥራቸውና ሕይወታቸው ሥራ በዝቶባቸው እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ስለ ሰጣት ራእይና ዕቅዶች ለማሰብ በሚቸገሩበት ጊዜ የሚከሰት ችግር ነው:: መንፈስ ቅዱስ ለማምጣት የሚፈለገውን ለውጥ ከማዳመጥ ይልቅ ነገሮች በተለመደው መንገድ እንዲቀጥሉ ማድረጉ ይቀልለናል::

በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለውጥ ለማምጣት የሚፈልጉ ሰዎች አዳዲስ ነገሮችን እንዳይሞክሩ በመከልከል የመንፈስ ቅዱስን ፍላጎት ሊቃወሙ ይችላሉ:: እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሳይሆን፣ የእርሱን ድምጽ በሚሰሙና ራሳቸውንና በአካባቢያቸው ያሉትን ሰዎች ለመለወጥ ፈቃደኛ በሆኑት ሰዎች አማካኝነት ለውጥን እንዳመጣ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንረዳለን:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነገሮች ባሉበት ሁኔታ እንዲቀጥሉ ስለምንፈልግ፣ መንፈስ ቅዱስ በሌላ ሰው በኩል የሚናገረውን ነገር ለመስማት እንፈልግም:: በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔር ተሐድሶን ለማምጣት ሌላ ሰው በሚጠቀምበት ጊዜ ይቀናሉ:: ስንት ጊዜ ነው

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በስጦታ የተካኑትን ወጣቶች አገልግሎት ወደ ዳር የሚገፉትና በዚህም ምክንያት ወጣቶችን ከቤተ ክርስቲያን የሚያርቁት? የሚያሳዝነው፣ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር በተለይ በቆዩት ቤተ እምነቶች ውስጥ የተለመደ መሆኑ ነው::

2. ቤተ ክርስቲያኒቱ በዕድሜ የገፉች ወይም ብዙ ምእመናን ያሏት ከሆነ፣ ለለውጥ ራሷን ክፍት የማድረግ አቅሟ አነስተኛ ነው:: ትውፊቶች ሥር ይሰድዳሉ:: ምንም እንኳን እነዚህ ትውፊቶች አብያተ ክርስቲያናት የመጡትን አዳዲስ አሳቦች ሁሉ እንዳያዳምጡ በማድረጉ በኩል ጠቃሚ ሚና ቢኖራቸውም፣ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ እንዳይሰሙና እግዚአብሔር በአዲስ ትውልድ ውስጥ ለመሥራት የሚፈስጋቸውን አዳዲስ ነገሮች እንዳያከናውኑ ሊያደርጉ ይችላሉ::

3. ዋናው የቤተ ክርስቲያን መሪ መንፈስ ቅዱስ ሰዎች እንዲለወጡና እንዲያድጉ የሚያቀርበውን ጥሪ መስማት አለበት:: ይህ አንዳንዶች «የለውጥ ሐዋርያ» የሚሉት ዓይነት ሰው መሆን አለበት:: መንፈሳዊ መሪ፣ «እግዚአብሔር በዘመናችን የሚፈልገው ነገር ምንድን ነው? ምን ዓይነት እድገት እንዲኖረን ይሻል?» የሚል ጥያቄ ለማንሣት ድፍረት ሊኖረው ይገባል:: መሪው ካለፉት ነገሮች ይማራል:: ነገር ግን እግዚአብሔር በዘመኑ አዳዲስ ነገሮችን እንዲያደርግ በመጠየቅ ወደ ፊትንም አሻግሮ ያያል (ኢሳ. 43:19)::

4. ለውጥ ለማምጣት የሚፈልግ የቤተ ክርስቲያን መሪ ከሌሎች ጋር በመተባበር ይህንኑ ማድረግ ይኖርበታል:: ዘለቄታዊ ለውጥ የሚመጣው ከአንድ ግለሰብ ውጭ ካለ ኃይል ሳይሆን፣ ነገር ግን ግለሰቡ ለመለወጥ እንዲፈልግ በማነሣሣት ነው:: በቀዳሚነት ይህንን የምናደርገው ሰዎች በሚከተሉት ነገሮች ላይ እንዲያተኩሩ በማገዝ ነው:- ሀ) መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከሕዝቡ እንደሚፈልግ በሚያስረዳው እውነቶች ላይ፣ እና ለ) ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሚፈልገውን እንዳትሆንና እንዳታደርግ የሚከለክሉ ችግሮች:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለሰዎች ጥያቄዎች መልስ በመስጠቱ ላይ ሳለማተኮር መጠንቀቅ አለባቸው:: ነገር ግን ጥያቄዎችን በማንሣት ምእመናን ራሳቸው ስለ ጉዳዩ እንዲያስቡ ማገዝ አለብን:: ሰዎች ለመለወጥ የሚፈልጉት ራሳቸው የእግዚአብሔርን ራእይ በሚመለከቱበት ጊዜ ነው::

5. ብዙውን ጊዜ ለውጥን በሚፈልጉና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ተደማጭነት ባላቸው ግለሰቦች አማካኝነት ለውጡን ማስተዋወቁ ጠቃሚ ነው:: መለወጥ ቢፈልጉ ሊያደርጉ ስለሚችሏቸው ነገሮች ብዙ ሰዎች በጥልቀት እንዲያስቡ ማድረጉ አስቸጋሪ ነው:: ነገር ግን ተደማጭነት ያላቸው ሰዎች ሌሎች እንዲለወጡ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ:: በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚፈልገውን ራእይ እንዲጨብጡ ማድረጉ ጠቃሚ ነው:: በተጨማሪም ይህ ቡድን ቤተ ክርስቲያን እንዳታድግ የሚከላከሉትን ችግሮች ለማወቅ አይቸገርም:: በመሆኑም፣ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ወደሚፈልግበት ደረጃ ለመድረስ ምን ማድረግ እንዳለባት ከዚህ ቡድን አስተያየቶች ሊመጡ ይችላሉ::

እነዚህ ተደማጭነት ያላቸው ሰዎች (ለምሳሌ፣ ተደማጭነት ያላቸው የወጣቶችና የሴቶች መሪዎች፣ ሽማግሌዎች) ወደ ቡድናቸው በመመለስ ስለ ለውጡ አስፈላጊነት ገለጻ አድርገው ሊያሳምኗቸው ይችላሉ:: ምእመናን ከሽማግሌዎች ለሚቀርቡ አሳቦች ጥርጣሬ የሚኖራቸው ሊሆን፣ ከቡድናቸው አባላት የተነሡትን አሳቦች ለመቀበል አይቸገሩም:: ተደማጭነት ያላቸው ሰዎች የመጣውን የለውጥ አሳብ ከተቀበሉ በኋላ፣ ከሽማግሌዎቹ በበለጠ በቀላሉ ቡድኖቻቸውን ለማሳመን ይችላሉ:: ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አምልኮ የሚካሄድበት መንገድ መቀየር አለበት የሚል እምነት ካላቸው፣ ከመዘምራን ቡድን አባላት ጋር አብረው መሥራት አለባቸው:: መዘምራኑ ካመኑበት፣ ከሽማግሌዎች በተሻለ ሁኔታ ወጣቶችን ለማሳመን ይችላሉ:: ቀድሞውንም ሽማግሌዎች ወጣቱ በሚፈልገው መንገድ እንዳያመልክ ተጽዕኖ ያሳድራሉ የሚል አስተሳሰብ ላለው ወጣት ይህ ጠቃሚ መንገድ ነው::

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያናችው እንድትሆንና እንድታደርግ በሚፈልገው መንገድ ማደግ አለብን

የሚል አቋም ያላቸው ሰዎች አሉ፡፡ በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእነዚህ ሰዎችና ከጓደኞቻቸው ጋር አብረው መሥራት አለባቸው፡፡ ቀድሞውንም እግዚአብሔር እንድንሆን የሚፈልገውን መሆን አለብን የሚል አቋም ያላቸውን ሰዎች በማሳመን፣ መሪዎች ለመለወጥ የሚፈልጉትን ሰዎች ቁጥር መጨመር ይችላሉ፡፡ ብዙ ሰዎች ለመለወጥ ፈቃደኛ በሚሆኑበት ጊዜ፣ የተቀረው ለውጡን ለመቀበል አይቸገርም፡፡

6. በአመዛኙ ሰዎች የሚያምኗቸውንና የሚያከብሯቸውን ሰዎች አሳብ ይቀበላሉ፡፡ በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሕዝቡ ጋር ቅርበት ያለውና በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት መፍጠር አለባቸው፡፡ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን የሚጋፈጧቸውን ችግሮች ማወቅና መረዳት አለብን፡፡ ምእመናን በራሳቸውና በመሪዎች መካከል ክፍተት አለ ብለው ካመኑ፣ ወይም መሪዎች ያለንበትን ሁኔታ አይረዱም ብለው ካሰቡ፣ የመሪዎቹን አሳብ ለመቀበልና ለመለወጥ ፈቃደኞች አይሆኑም፡፡

7. አብዛኞቹ ሰዎች ለውጥን ይቃወማሉ፡፡ እንዲሁም ደግሞ ለውጡ ከፍተኛ ወይም አደገኛ በሚሆንበት ጊዜ፣ የበለጠ ይቃወሙታል፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዕቅዶቻቸው ውስጥ ምእመናን የትኞቹን ነገሮች እንደሚቃወሙ ለመረዳትና እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር በማድረግ የሚያገኟቸውን ጥቅሞች አብራርተው ለማሳመን የሚችሉባቸውን መንገዶች ማለብ ይኖርባቸዋል፡፡ መሪዎች የአብዛኞቹን ምእመናን አሉታዊ አስተሳሰብ ለመለወጥና በእምነት ዓይኖቻቸው ወደ እግዚአብሔር በመመልከት የለውጥን ኃይል ከእርሱ ዘንድ እንዲቀበሉ ለማግባባት መጣር አለባቸው፡፡

8. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን የሚያድጉባቸውን ደረጃዎች ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ ምእመናን እግዚአብሔር ከሚፈልገው የለውጥ ደረጃ ላይ መድረስ ከባድ ነው የሚል እምነት ካላቸው፣ ለመለወጥ አይሞክሩም፡፡ ወይም ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪው ስኬታማ የማይሆኑ ታላላቅ የለውጥ አሳቦችን አምጥቶ ከሆነ፣ ሕዝቡ አዳዲስ ነገሮችን ለመለወጥ ፈቃደኛ ሳይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ምእመናን ነገሮቹ የሚቻሉ መሆናቸውን ካመኑ፣ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር ለማድረግ የበለጠ ተነሣሽነት ይኖራቸዋል፡፡

የቤተ ክርስቲያን ምእመናን እግዚአብሔር የሚፈልገውን ነገር በማድረጋቸው የሚያገኟቸውን ጥቅሞች (ዘላለማዊ ጥቅሞች) መረዳት አለባቸው፡፡ ሰዎች አንድ ነገር እንዴት እንደሚጠቅማቸው ካላወቁ፣ እርምጃ ለመውሰድ ይቸገራሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ምእመናን አዲስ ከመጣው አሳብ ጋር አለመስማማታቸውን ለማሳየት በቀጥታ ከመቃወም ይልቅ ለተግባራዊነቱ ተባባሪ ከመሆን ይቆጠባሉ፡፡

9. ለመለወጥ ፈቃደኛ የሆኑ በቂ ሰዎች ሲገኙ፣ በተቻለ ፍጥነት ለውጡን እውን ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ዕቅዶች ማውጣትና አስፈጻሚ ሰዎችን መመደብ ያስፈልጋል፡፡ ሰዎች ለውጡን ለማካሄድ ስሜታዊ ዝግጅት ካደረጉ በኋላ ተግባራዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ብዙ ጊዜ መጠበቅ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜ ካለፈ፣ ለመለወጥ የነበራቸውን ተነሣሽነት ሊያጡና ወደ ነበሩበት ሁኔታ ሊመለሱ ይችላሉ፡፡

10. ሰዎች ከለውጡ ጋር እንዲላመዱና አዲሱን ተግባር እስኪተዋወቁ ድረስ ለውጦቹ መደጋገም አለባቸው፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዘለቄታዊ ለውጥ ለማምጣት ከፈለጉ፣ አንድ ጊዜ ብቻ ሥራውን ካከናወኑ በኋላ ወደ ሌሎች ጉዳዮች መግባት የለባቸውም፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚያስተዋውቋቸው ብዙ ነገሮች ስኬታማ የማይሆኑት ከሕዝቡ ጋር እስኪዋሃዱ ድረስ በተደጋጋሚ ጥረት ስለማይደረግባቸው ነው፡፡ መጀመሪያው ላይ አሳቡ ተቀባይነት ያገኝና፣ መሪዎች ወደ ሌሎች ጉዳዮች በፍጥነት ይሸጋገራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ምእመናን ወደ ቀድሞው ሁኔታቸው ይመለሳሉ፡፡ (ለምሳሌ፣ የደቀ መዝሙርነት እያያዝ ለውጥ ያስፈልገዋል የሚል እምነት ያላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስለዚሁ ጉዳይ ሥልጠና ይሰጣሉ፡፡ ምእመናንም ከትምህርቱ ጋር ይስማማሉ፡፡ ነገር ግን የተሰጠው ትምህርት ተግባራዊ ስለማይሆን ለውጥ አይመጣም፡፡) ለመለወጥ የሚፈለገው ልምምድ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ለረዥም ጊዜ የቆየ ከሆነ፣ አዲሱን ልምምድ ለ

ረዥም ጊዜ መቀጠል ያስፈልጋል። የሰው ልጅ ወደ ለመደው ነገር የመቀየስ ዝንባሌ አለው። ለረዥም ጊዜ የተደጋገሙ ተግባራት ወይም እምነቶች ለማስወገድ የሚከብዱ ነገሮች ናቸው። አዲሱ ልምምድ ተቀባይነት አግኝቶ ተግባራዊ እስኪሆን ድረስ በተደጋጋሚ ማስተማርና ማሳየት ያስፈልጋል። (ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመናን በየሳምንቱ ለአንድ ሰው የሚመሰክሩበትን ሁኔታ ለማስለመድ ከፈለጉ፣ አንድ ጊዜ ብቻ መመስከር አለባችሁ ብሎ ማለፍ ሳይሆን፣ በየሳምንቱ ስለዚሁ ጉዳይ ምእመናንን ማደፋፈሩ ጠቃሚ ይሆናል። እንዲሁም ደግሞ ለዎች ምስክርነት በሚሰጡበት ጊዜ ያጋጠሟቸውን ነገሮች እንዲመሰክሩ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። ሽማግሌዎች ለስድስት ወራት ይህንኑ ተግባር ቢያካሂዱ፣ ለዎች የመመስከርን ልማድ ያዳብራሉ። ይህ አንድ ጊዜ መመስከር አለባችሁ የሚል ትምህርት ሰጥቶ ከመተው የበለጠ ዘላቂ ውጤት ሊያመጣ ይችላል።) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አዲስ ለውጥ ከማምጣታቸው በፊት፣ የፊተኛው ለውጥ በአማኞች ልብ ውስጥ መስረጹን ማረጋገጥ አሰባቸው። ይህ ካልሆነ፣ ለዎች ቀደም ሲል ያደርጉት ወደ ነበረው ሁኔታ ይመለሳሉ።

መሪዎች ብዙ ነገሮችን በአንድ ጊዜ ለማድረግ በመፈለጋቸውም ምክንያት ብዙ የለውጥ ጥረቶቸ እንደሚመክኑ መረዳቱ ጠቃሚ ነው። የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በአንድ ጉዳይ ላይ ትኩረት ስለማያደርጉ ለውጦቹ እውን አይሆኑም።

11. እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሁሉም ሰዎች (ለመለወጥ የሚፈልጉት ብቻ ሳይሆን) እረኞች እንዲሆኑ ጠርቷቸዋል። አንዳንድ ለዎች የቀረበውን የለውጥ እሳብ ሁሉ የመቃወም ዝንባሌ ሊኖራቸው ይችላል። ብዙውን ጊዜ ሰዎች ለረዥም ዓመታት የተለየ ነገር ሲያደርጉ ከኖሩ በኋላም ሳይቀር፣ «ድሮ ቀረ» እያሉ የጥንቱን ሲናፍቁ እንሰማለን። ብዙ ሰዎች እምነታቸውንና ተግባራቸውን በሚቀይሩበት ጊዜ፣ ለውጡን የሚቃወሙ ሰዎች ይበልጥ ተቃውሟቸውን ያጠነክራሉ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በለውጥ ፈላጊዎች ላይ ትኩረት በማድረጋቸው



ምክንያት እነዚህን ወገኖች ቸል ከማለት ይልቅ፣ እነዚህንም ለዎች መውደዳቸውን መቀጠል አለባቸው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የኋላ ኋላ እነዚህ ሰዎች ለውጡን እንዲቀበሉ ማድረግ የሚችሉት ትችቶቻቸውን በመስማትና በትዕግሥት ፍቅራቸውን በማሳየት ብቻ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው፣ ፍቅር መታገሥ ነው - ሰዎች እስኪያድጉና እስኪለወጡ ድረስ ይጠብቃልና (1ኛ ቆሮ. 13:4)። ፍቅር እንዲህ ዓይነት ሰዎችን አላስፈላጊዎች አድርጎ አይቆጥራቸውም። በእድገት ሂደት ሁሉ ውስጥ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የክርስቶስን አካል አንድነት መጠበቅ አለባቸው። ክፍፍል እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የወጠነውን ዕቅድ የሚቃረን ተግባር ከመሆኑም በላይ፣ ዘለቄታዊና እግዚአብሔርን የሚያስከብር ለውጥ እንዳይመጣ ይከላከላል።

19ኛ ጥያቄ:- የቤተ ክርስቲያናችሁን መዋቅር በመቀየር እያንዳንዱ ምእመን አሥር አባላት የሚገኙበት ቡድን አባል በመሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የጸሎት ፕሮግራም እንዲያካሂድ ትፈልጋለህ እንበል። ከላይ የተሰጠውን ትምህርት በመከተል፣ እንዴት ለውጥ ለማምጣት እንደምትሞክር ግለጽ። ይህንን ለውጥ ለማምጣት የምትጠቀምባቸውን ደረጃዎች ግለጽ።

## ሦስተኛ ቀን

ተክለአብ ለረዥም ጊዘ በመሪነተ ሲያገለግል ቆይቷል። ልጅ ሳለ መሪዎች ውሳኔ ሲሰጡ፣ ሕዝቡ አድርጉ የተባሉትን ብቻ ነበር የሚያደርጉት። ሕዝቡ አንድን ነገር ለምን እንደሚያደርጉ መረዳት አያስፈልጋቸውም ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰዎች የመሪውን ትእዛዝ መፈጸም እንዳለባቸው ያውቃሉ። ከዚያ በኋላ ግን አዲስ ትውልድ መጣ። ከእነዚህ ምእመናን ብዙዎች ትምህርት ቤት የመግባት ዕድል የነበራቸው ናቸው። ዜና የማዳመጥ፣ ጋዜጣ የማንበብና አንድን ነገር ለምን እንደሚያደርጉ መጠየቅ የለመዱ ናቸው። ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚመጡትን ትእዛዛት ዝም ብለው የሚቀበሉ ዓይነት አልነበሩም። ውሳኔ የመስጠቱ ሂደት አካል ለመሆን ይፈልጋሉ። በመሆኑም፣ ተክለአብ ወጣቶችንና የተማሩትን መሪዎች ከቤተ ክርስቲያን አባረረ። ከማኅበረ ምእመናኑ

ሁኔታ ጋር ራሱን ለማስተካከል ባይችልም፣ ተክለአብ ለእግዚአብሔርና ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ሠርቶ ነበር:: በቀጣዩ ዓመት ተክለአብ ለመሪነት ሳይመረጥ ቀረ:: ሕዝቡ የመሪዎቹን ውሳኔዎችና ውሳኔዎቹ የተሰጡባቸውን ምክንያቶች የሚያብራራ መሪ ነበር የፈለገው::

**20ኛ ጥያቄ፡- ሀ)** የቤተ ክርስቲያን ምእመናን መረጃ ለማወቅ፣ ውሳኔዎች የሚሰጡባቸውን ምክንያቶች ለመረዳትና የውሳኔ ሰጭነቱ ሂደት አካል ለመሆን ሲፈልጉ የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) ከሰዎች ጋር በጥሩ ሁኔታ የሚግባባው መሪ ጥሩ መሪ ለመሆን ሲችል፣ ለመግባባት ያልቻለው ደግሞ ጥሩ መሪ ለመሆን የማይችለው ለምንድን ነው? ሐ) የመግባባት ክህሎት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስፈላጊ የሚሆኑባቸውን አንዳንድ ምክንያቶች ዘርዝር::

ጥሩ አመራር በባሕርይ ላይ እንደሚመሠረት ተመልክተናል:: ሰዎች የሚያከብሯቸውን ሰዎች ለመስማትና ለመከተል ይፈቅዳሉ:: ስለሆነም፣ አንድ ሰው መሪ ከመሆኑ በፊት፣ መንፈሳዊ ባሕርይ ሊኖረው ይገባል:: እንዲህ ዓይነቱ ባሕርይ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው እንዲሠራ ከማስቻሉም በላይ፣ ምእመናን ምሳሌነታቸውን እንዲከተሉ ያስችላቸዋል:: ውጤታማ መሪ ለመሆን፣ አመራራችንን ፍሬያማ የሚያደርጉትን ክህሎቶች መላበስ እንዳለብንም ተመልክተናል:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኖቻችንን በከፍተኛ ደረጃ ለመለወጥ እንዲጠቀምብን ከፈለግን፣ ለቤተ ክርስቲያናችን ራእዮችን እንደ መተለም፣ ጥራት ያላቸውን ዕቅዶች እንደ ማውጣት፣ በአግባቡ ሥራዎችን ለሰዎች በውክልና እንደ መስጠት፣ ከምእመናን ጋር መልካም ግንኙነት እንደ መፍጠር፣ ጥሩ ውሳኔዎችን እንደ መስጠት የመሳሰሉትን ክህሎቶች መማር አለብን::

ነገር ግን ለአመራር መሠረታዊ የሆነ ሌላ ክህሎት አለ:: ያለዚህ ክህሎት አመራር ውጤታማ ሊሆን አይችልም:: በሰው ሰውነት ውስጥ ያለው ደም የግለሰቡ ሰውነት በአግባቡ እንዲሠራ እንደሚያደርግ ሁሉ፣ የድርጅቶች አሠራር ስኬታማ እንዲሆን የሚያስችለው ተግባቦት ነው:: በአመዛኙ በመሪዎች ወይም በመሪ



ዎችና በሕዝቡ መካከል አለመግባባትና አለመተማመን እንዳይኖር የሚያደርገው የተግባቦት አለመር ነው:: ይህም የመሪዎች ሥራ ውጤታማ እንዳይሆን ይገድባል:: መሪዎች ከምእመናን ጋር ለማከናወን የሚፈልጓቸው ብዙ ሥራዎች የማይሳኩትም መረጃዎች በግልጽ ባለመተላለፋቸው ነው::

**21ኛ ጥያቄ፡- ሀ)** መሪዎች አንድን መረጃ ለሕዝቡ አለማስተላለፋቸው በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ችግር የፈጠረበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) ዘፍጥ. 11፡1-9ን አንብብ:: 1) እግዚአብሔር ያልተደሰተበት ሁኔታ ምን ነበር? 2) እግዚአብሔር ሰው በእርሱ ላይ እንዳያምፅ ገደብ ለመጣል ምን አደረገ?

*በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውጤታማ አገልግሎት የማይካሄደውና ክፍፍል የሚፈጠረው ጥሩ ተግባቦት ባለመኖሩ ነው::* በዘፍጥ. 11:1-9፣ ሰዎች ተነጋግረው መግባባት በሚችሉበት ወቅት አስደናቂ ነገሮችን፣ በተለይም ትልልቅ ክፉ ነገሮችን፣ ለማድረግ ይችሉ ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር ሰዎች በእርሱ ላይ የሚያምፁበትን መንገድ ለመገደብ ስለ ፈለገ፣ እርስ በርሳቸው የሚግባቡበትን ሁኔታ ቀነሰ:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በቤተ ክርስቲያኖቻችን ብዙውን ጊዜ የስምምነት ግንኙነቶችና ውጤታማ አገልግሎት እንዳይኖር የሚያደርገው የተግባቦት ጉድለት ነው:: እንዲያውም፣ የተግባቦት እጥረት በአመራርና አስተዳደር ውስጥ ከሚያጋጥሙት ታላላቅ ችግሮች አንዱ ነው::

## ክህሎት ሰባት፡- እንደ አገልጋይ መሪ እንዴት ከሰዎች ጋር መግባባት እንደሚቻል ማወቅ

**ሰዎች ብዙውን ጊዜ የአንድን ሰው የአመራር ችሎታ ለማወቅ የመግባባት ችሎታውን ያያሉ::**

አንድ መሪ የእግዚአብሔርን ራእይ ተረድቶ ራእዩን እውን ለማድረግ የሚያስችሉትን ዕቅዶች በመንደፉ በኩል ጎበዝ ሊሆን ይችላል:: ወይም ደግሞ ከግለሰቦች ጋር ግላዊ ግንኙነት የመመሥረት ብቃት ሊኖረው ይችላል:: ነገር ግን ከፍተኛ የመግባባት ችሎታ ከሌለው፣ ብዙ ሰዎች መሪ ሊሆን ይችላል ብለው አይገምቱትም:: ሰዎች ለመሪነት የሚጠቀሙት ውጤታማ

የመግባባት ችሎታን ነው:: አብዛኞቹ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመሪነት የተመረጡት የመግባባት ችሎታ ስላላቸው ነው:: በስብሰባዎች ላይ አንድ ሰው ብድግ ብሎ በስሜታዊነት የሚፈልገውን አሳብ ለመናገር ከቻለ፣ ብዙ ሰዎች ለመሪነት ያጩታል:: ነገር ግን አንድ ሰው ዓይናፋርና ዝምተኛ፣ በሰዎች ፊት የማይናገር ከሆነ፣ ሌሎች ከፍተኛ ችሎታዎች ከሌሉት በቀር ለመሪነት ላይመረጥ ይችላል:: ስለሆነም፣ የተግባቦት ክህሎት አስፈላጊ ነው ማለት ነው:: እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ሰዎችን ለመሪነት ለማስነሣት ይህንን ክህሎት ይጠቀማል::

መልካም ተግባቦት የሁሉም አመራር መሠረት ነው:: የመልካም ተግባቦት አለመኖር ደግሞ በአመራር ውስጥ የአብዛኞቹ ችግሮች መሠረት ነው::

ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎት ጥሩ ተግባባት ወሳኝ ከሚሆንባቸው ነገሮች መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ:-

- ምእመናን እንደ ራሳቸው ራእይ እንዲመለከቱና እንዲቀበሉ ለማድረግ የቤተ ክርስቲያንን ራእይ በጥሩ ሁኔታ ለምእመናኑ ማስተላለፍ ያስፈልጋል:: ይህ ካልሆነ፣ ራእዩ በመሪዎች ውስጥ የሚገኝ አሳብ ከመሆን አያልፍም:: አንድ አሳብ ወደ ሌሎች የሚተላለፈው በተግባቦት ነው:: ተግባቦት አንድ አሳብ ተግባራዊ እንዲሆን ያስችለዋል::

- መልካም ተግባቦት ከሌለ፣ በአማኞች መካከል የሚፈጠሩ ብዙ አለመስማማቶች ሊፈቱ አይችሉም:: በእኛና በሌላ መሪ፣ ወይም በተለያዩ ቡድኖች መካከል ያሉትን አለመግባባቶች ለመፍታት ብንፈልግም፣ ጥሩ የመግባባት ችሎታ ከሌለን፣ ዕርቅን ለመፍጠርና በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ሰላም እንዲኖር ለማድረግ እግዚአብሔር ላይጠቀምብን ይችላል::

- መልካም ተግባቦት ሳይኖር ከሌሎች መሪዎችም ሆነ ምእመናን ጋር ጥሩ ግንኙነት ሊኖረን አይችልም:: ሌሎች ከእኛ ርቀው ስለሚቀሩ፣ እንደ ጥሩ ቡድን የእግዚአብሔርን ራእይ ለመፈጸም አብረን ልንሠራ አንችልም::



- መልካም ተግባቦት ሳይኖር ምእመናን እንዲተማመኑብንና እንዲያከብሩን፣ ከዚህም የተነሣ አሳባችንን እንዲያዳምጡና እንዲከተሉን ልናደርግ አንችልም::

- መልካም መግባባት ከሌለ፣ መሪዎች፣ ኮሚቴዎችና ቦርዶች ጥሩ ውሳኔዎችን እንዲያደርጉ ሊመሯቸው አይችሉም::

- መልካም መግባባት ከሌለ፣ ከሌሎች ጋር እንደ ቡድን ልትሠራና የእግዚአብሔር ሥራ በጥሩ ሁኔታ እንዲከናወን ልታደርግ አትችልም::

ስለሆነም፣ ውጤታማ ተግባቦትን ለመቀዳጀት መማሩ ለአንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ስኬታማነት ወሳኝ ነው::

## እውነተኛ ተግባቦት የሚያካትታቸው ነገሮች:-

ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው አንድን መረጃ ለሌላው የሚያስተላልፍበትን ሁኔታ ለመግለጽ ተግባቦት የሚለውን ቃል እንጠቀማለን:: በመሆኑም፣ ስንናገር ወይም ስንጽፍ፣ ከሰዎች ጋር እየተግባባን ነው ብለን እናስባለን:: ሬድዮ ስናዳምጥ ወይም ቴሌቪዥን ስንመለከት፣ መግባባት እየተካሄደ ነው ብለን እናስባለን:: ስለ ተግባቦት ስናስብ፣ ንግግር በሚያደርገው ሰው ላይ ትኩረት እናደርጋለን:: ስለሆነም፣ ስንሰብክ ወይም ማስታወቂያዎችን ስንናገር፣ መግባባትን እየፈጠርን ነው ብለን እናስባለን::

ነገር ግን ንግግር ከመግባባት ጋር አንድ አይደለም:: እንበልና፣ ብድግ ብዬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በእንግሊዝኛ ስብከት አደረግኩ:: ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚሰማ ሰው አልነበረም:: በዚህ ጊዜ መግባባት ይቻላል? በፍጹም አይቻልም:: ቃላት ከአፌ መውጣታቸውን ይቀጥላሉ:: እነዚህም በሆነ ዐውድ ውስጥ ሰዎች የተወሰነ መልእክት እንዲያገኙ የሚያስችሉ ይሆናሉ:: (ለምሳሌ፣ ሰዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ በሚነጋገሩበት አሜሪካ አገር ውስጥ ብሆን፣ መልእክቱን ይሰሙኝ ነበር::) ነገር ግን ማንም ሰው እንግሊዝኛ በማይሰማበት ቦታ መግባባት አይቻልም:: እንዲያውም፣ ለስብከት የማደርገው ጥረት

ሁሉ ጊዜ ማባከን ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም፣ ተግባቦት መናገር ብቻ ሳይሆን፣ አንድ ሰው መልእክቱን ሌላው በሚረዳበት መንገድ **የሚያቀርብበት** ነው::

ሰዎች ብዙውን ጊዜ ይህንን እውነት ስለማይረዱ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረገው አብዛኛው ነገር ጊዜ ማባከን ሆኖ ይገኛል:: ለምሳሌ፣ መዘምራን ቢዘምሩና ነገር ግን የሙዚቃው ድምጽ በጣም ከፍ በማለቱ ምክንያት ምን እየተናገሩ እንደ ሆነ ሕዝቡ ባይሰማቸው፣ መግባባት እየተፈጠረ ነው ማለት አይቻልም:: ሕዝቡ የመዝሙሩን ፍች ሳያገኝ ይችላልና:: አንዳንድ ጊዜ ብዙ ሰዎች አማርኛ በማይናገሩባቸው የገጠር አካባቢዎች መዘምራን የአማርኛ መዝሙር ሊዘምሩ ይችላሉ:: መዘምራኑ ይህንን በማድረጋቸው መግባባትን ፈጥረናል ብለው ሊያስቡ ቢችሉም፣ ሰዎች የአማርኛ ቃላት ስለማይሰሙ፣ መግባባት አይቻልም:: በ1ኛ ቆሮንቶስ 14 ውስጥ ሐዋርያው ጳውሎስ በሕዝባዊ አምልኮ ላይ የማይተረጎሙ ልሳናትን መናገር ተገቢ እንዳልሆነ ይናገራል:: ለዚህም ምክንያቱ መግባባት ሊፈጠር ስለማይችል ነው:: በዚህ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች ከአእምሮአቸው ውስጥ የሚቀር መረጃ ሊያገኙ አይችሉም:: ይህ ማንም የማይረዳውን ድምጽ እንደሚሰጥ መለከት መሆኑ ነው (1ኛ ቆሮ. 14:6-12)::

ስለሆነም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊረዱ ከሚገባቸው እጅግ ጠቃሚ ነገሮች አንዱ አንድን ነገር በመናገራችን ብቻ መግባባት ላይፈጠር እንደሚችል ነው:: መግባባት ሊፈጠር የሚችለው የተነገረውን ነገር የሰሙት ሰዎች ሲረዱ ነው:: ነገር ግን ሰሚዎቹ የሚነገረውን ነገር ባለመስማታቸው፣ ቋንቋው ሰሰ-ማይገባቸው፣ ንግግሩ አሰልቺ በመሆኑ፣ ወይም በባህሉ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውን የአነጋገር መንገዶች (ለምሳሌ፣ ታሪኮች፣ ምሳሌዎች፣ ቀልዶች) ባለመጠቀሙ ምክንያት ሰሚዎቹ ጆሮ ባይሰጡ፣ ከቃላት መነገር በቀር የመልእክት ልውውጥ አልተደረገም:: **በተናጋሪው አእምሮ ውስጥ ያለው መረጃና በልቡ ውስጥ ያለው ስሜት በአድማጩ ግንዛቤ እስካላገኘ ድረስ፣** *መግባባት አልተካሄደም*::



22ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ ሰው መግባባት የሌለባቸውን ቃላት በመናገሩ ምክንያት የተከሰተውን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) መግባባት እንዳይካሄድ ያደረገው ችግር ምንድን ነበር?

እውነተኛ መግባባት ሲካሄድ የሚችለው የሚከተሉት ነገሮች ሲኖሩ ነው:-

1. በአእምሯችን ውስጥ ያለው ፍች ለምንናገራቸው ሰዎች በትክክል ሲተላለፍ:: አሳባችን አድማጩ ከተረዳው ውጭ ከሆነ፣ መግባባት አልተካሄደም ማለት ነው:: «ነገ እመጣለሁ፣» ብልና፣ አድማጮቹ፣ «ዛሬ እመጣለሁ፣» እንዳልኩ አድርገው ቢገነዘቡ፣ ተናግሬአለሁ እንጂ መልእክቱን አላስተላለፍኩም:: «ኢየሱስ ይወዳችኋል፣» ብልና፣ እነርሱ ግን፣ «ኢየሱስ ጥሩ ነገር የሚሠሩትን ሰዎች ብቻ ይወዳል፣» የሚል ግንዛቤ ቢወስዱ፣ መልእክቴን አላስተላለፍኩም ማለት ነው:: ስለሆነም፣ ሰዎች በአእምሯችን ውስጥ ያለውን ፍች እንዲወስዱ ለማድረግ ጥረት ማድረግ አለብን::

2. በድርጊታችን የምናስተላልፈው መልእክት የአፋችንን ቃል ማጠናከር አለበት:: መልእክትን የምናስተላልፈው በአፋችን ብቻ ሳይሆን፣ በድርጊታችንና ከፊታችን ላይ በሚታዩ ምልክቶች ጭምር ነው:: እንዲያውም፣ ምሁራን እንደሚሉት፣ አብዛኛው መልእክት የሚተላለፈው ቃላዊ ባልሆነ መንገድ ነው:: በአፋችንና በድርጊታችን የምናስተላልፋቸው መልእክቶች ካልተጣጣሙ፣ ሰዎች ከቃላችን ይልቅ «ድርጊታችንን» ወደ መስማቱ ያዘነብላሉ:: ለምሳሌ፣ «ኢየሱስ ቅዱሳን እንድትሆኑና ከጋብቻ ውጭ ወሲብ እንዳትፈጽሙ ይፈልጋል፣» ብንልና ነገር ግን ሰሚዎቹ ከጋብቻ ውጭ ወሲብ እንደምንፈጽም ቢያውቁ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ፈቃደኞች ላይሆኑ ይችላሉ:: ለምሳሌ፣ የግንኙነት ችግር ካለብን ሰው ጋር እየተነጋገርን ነው እንበል:: ግለሰቡን ላለማየት ስንል ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንመለከታለን:: ይህም ድርጊት እውነት እየተናገርን አለመሆናችንን ሊያሳይ ይችላል:: አንድ ሰው ከእኛ ጋር ቢነጋገርና እኛ ግን መሬት መሬት ብናይ ወይም በመስኮት ወደ ውጭ ብንመለከት፣ ድርጊታችን የሚያሳየው ለመስማት